


[illegible] ጎንደር [illegible] ቅዱስ ሚካኤል [illegible] ቤተ ክርስቲያን

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

ዋጋ ፩ ብር



በትዕዛዝት ጎንደር የሚመኝ ቤት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

ቁጥር ፳፩፯

ሰኔ ፲፱፻፹ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጉሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »


ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣን ወርቅ በዛብህ

ም. አዘጋጅ መ/ ክንፈ
ርግብ ማርቆስ


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤


# ማውጫ

## አርእስት


| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ርእሰ አንቀጽ (ሞኝ የዕለቱን ብልህ የዓመቱን) | ፪ |
| መንፈሳዊ ሹመት | ፬ |
| ዋና ሥራ አስኪያጁ በወሎ የሕፃናት ማሳደጊያዎችን ጐበኙ | ፯ |
| ሥራ ሕይወት ነው | ፯ |
| ማስተማር አምላካዊ ትእዛዝ ነው | ፰ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፱ |
| ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት | ፲፩ |
| የጻድቁ የአቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ ታሪክ በአጭሩ | ፲፪ |
| ቅድስት አርሴማ | ፲፯ |
| ዜና ቤተ ክርስቲያን | ፲፱ |
| የቅዱስ ላሊበላ ቅርስ | ፳፩ |
| ትንሣኤና ሕይወት | ፳፫ |


ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ ፤

እንደምን አላችሁ ። እኔ የመንፈስ ቅዱስ ወንድማችሁ ለእናንተ ሰላም ፤ ፍቅር ፤ ደኅንነት ፤ ጥሩ የሆነ የሥራ ፍሬ እንዲሆንላችሁ ከልብ እመኝላችኋለሁ ። ከከበረው ሰላምታዬ በመቀጠል የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቅርቢያለሁና መልሱን በትዕግሥት እጠብቃለሁ ።

፩ኛ በጽሑፍ ተደግፈው የሚታተሙ ፎቶ ግራፎች እጅግ በጣም የሚያስደስቱ ስለሆኑ በሚታተሙ ጽሑፎቻችሁ ሁሉ ፎቶ ግራፍ ከመጨመር ወደ ኋላ እንዳትሉ አደራ ፤

፪ኛ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደሌሎቹ ድርጅቶች በራዲዮ ፤ በቴሌቪዥንና በመሳሰሉት በማምንት አንድ ቀን ፕሮግራም ለምን አይሰጣትም ፤ ይህንን ለማዘጋጀት ዕቅድ አለ ወይ?

፫ኛ የሰበካ ጉባኤ የሚለው መጠሪያ ስም ቀርቶ ሌላ ስም ቢሰጠውስ ማለትም ሰበካ ጉባኤ ሲባል ስሙ ለምእምናን ስለማይገባ በሌላ ስም እንዲጠራ ለምን አይደረግም ?

፬ኛ ለሐዋርያት በተሠጠው ማሠርና መፍታት ሥልጣን መሠረት ቄሱም ማሠርና መፍታት እንደሚችል ሁላችንም ተምረን እውቀናል ። ነገር ግን ቄስ ምእመኑን የማይገባ ሥራ ሲሠራ አግኝቶ ቢያወግዘው ምእመኑ መልሶ ሊያወግዘው ይችላልን?

፭ኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰቀል ወደ መስቀያው ቦታ በአይሁድ እጅ ተይዞ ሲወሰድ ሴቶች ደረታቸውን እየደቁ እያለቀሱ ወደ ቤታቸው ተመለሱ ይላል ። በዚህ ልማድ የሀገራችን ሴቶች ዘመድ ሲሞትባቸው ደረታቸውን እየደቁ ለሞተው ወገናቸው ያለቅሳሉ ። ይህንኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ትቀበለዋለች ወይ ?

፮ኛ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ብዛት ወደ ስንት ቁጥር ተጠግቷል ይህንን ብታብራሩልኝ አመሰግናለሁ ።

፯ኛ የሰንበት ት ቤት ኃላፊ እየተዘዋወሩ ስሚናር የሚሰጡ ሰዎችን መድቦ በአንድ አንድ ክፍለ ሀገር ሲሚናር ማካሄዱን ሰምተናል ። ወደ ጋሞ ጎፋ ክፍለ ሀገር መጥቶ ለምን ሰሚናር አላደረገም? ጠይቃችሁ ምክንያቱን በትንሣኤ መጽሔት አብራሩልኝ።

ዲያቆን ገዛኸኝ ደረሰ
ጋሞ ጎፋ ሀ ስብከት
አርባ ምንጭ ከተማ
ከፍተኛ ፪ ቀበሌ ዜሮ ፬
ከቅ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን
የሰ ተማሪዎች።

* * *

መልስ

ዲያቆን ገዛኸኝ ደረሰ ስላቀረብክልን መንፈሳዊ ሰላምታ እያመሰገን ላቀረብካቸው ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን ።

በመጀመሪያው ጥያቄህ ከጽሑፎችን ጋር ፎቶ ግራፍ ማውጣትን እንዳንተው ያሳስባል ፤ እንዳልከው ለጹሑፎችን የሚስማማ ፎቶ ግራፍ ካገኘን በጽሑፎችን ተጨማሪ ፎቶ ግራፍ ከማውጣት የማናቋርጥ መሆናችን ለጠያቂው ለማረጋገጥ እንወዳለን ።

በሁለተኛው ጥያቄህ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ትምህርት ለመስጠት በቤተ ክርስቲያን በኩል ዕቅድ መኖሩን አለመኖሩን እንድናስረዳህ ጠይቃሃል ፤ እስከ አሁን ድረስ የምናውቀው ነገር የለም ዕቅድ ከወጣ ግን ወደፊት በመጽሔቶችና በጋዜጦች ለመግለጽ ዝግጅች ነን ።

በሶስተኛው ጥያቄ ሰበካ ጉባኤ የሚለው ቃለ ለምእመናን ስለማይገባ እንዲለወጥ የሚጠይቅ ነው ሰበካ ጉባኤ ማለት በአንዲት ቤተ ክርሲቲያን ሰበካ (አጥቢያ) የሚገኙ መእመናን አንድነት ማለት ነው ። ሰበካ ጉባኤ የሚለው ቃል ይለወጥ ከማለት ይልቅ ትርጓሜው ተመላልሶ ይጻፍ ለምእመናን አይገባቸውምና ማለቱ ይሻል ይመስለናል ።

ስለዚህም ዲያቆን ገዛኸኝ ሰበካ ጉባኤ የሚለው ቃል የማይገባቸው ምእመናን ካሉ አንተም እኛም ሌሎችም ትርጉሙ የገባቸው ተባብረን ለምእመናን ማሳረዳት አለብን እንጂ ቃሉ ይለወጥ ልንል አይገባንም ። ስለዚህ እሁ

(ወደ ገጽ ፳፬ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

# ርእሰ አንቀጽ

## ሞኝ የዕለቱን ብልህ የዓመቱን

መተርጕማነ መጻሕፍት ሊቃውንት ባሕታውያን የዕለቱን ፡ ሰብአ ዓለም የዓመቱን ማሰብ ይገባቸዋል ይላሉ ። ነገር ግን አሳብ ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ቀዳሚ ስለሆነ የሰው አሳብ በዘመን ሊወሰንና ሊገታ አይቻልም ። እንደ እውነቱ ከሆነ ሰው ማሰብ ያለበት እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ነው ።

ይህንም ስንል ዕለተ ሞትን እያወጡና እያወረዱ ከተግባረ ሥጋ መቦዘን ያስፈልጋል ማለታችን እንዳልሆነ ለማሳሰብ እንሻለን ። ሥጋን ከለበሱ ሞት የማይቀር ዕዳ ነው ። ለሞት መድኃኒት የለውም ። መድኃኒቱ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ሕያው የሆነ ሥራ ሠርቶ ማለፍ ነው ወደኋላ መለስ ብለን ታሪክን ስንመለከት በቅዱስ መጽሐፍ የተመዘገበ ብዙ ሰዎችን እናገኛለን ። በቅዱስ መጽሐፍ ተመዝግበው ከሚገኙትም ሰዎች መካከል ብዙዎቹ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የፈጸሙና በሕጉ ጸንተው የኖሩ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለማፍረስ በተንኮል ሲታገሉ በክፋ አወዳደቅ የወደቁና የተቀጡ ናቸው ።

ለምሳሌ ኖኅ ከእነ ቤተ ሰቡ ከጥፋት ውሃ ሲድን ሰብአትካት ጠፍተዋል ... እንዲሁም ሰብአ ሰዶም ሰብአ ገሞራ በእሳት ሲቃጠሉ ሎጥ ከቤተ ሰቡ ጋር ለመዳን ችሏል ፤

"በጥቃ መዓቱ ሀሉ ብዙኅ ምሕረቱ" በመዓቱ አጠገብ ብዙ ቸርነቱ አለ ተብሎ እንደተጻፈው እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ይቀጣቸዋል እንጂ ፈጽመው እንዲጠፉ አያደርጋቸውም ።

ታሪክን እየተመለከቱ ለመልካም ታሪክ ባለቤት ለመሆን መጣር የአስተዋዮች ተግባር ነው ። እግዚአብሔርን በፍጹም ልባቸው ያገለገሉ ቅዱሳን ሰዎች ነፍስና ሥጋቸው ሳይለያይ በቁመናቸው በቅተው ተሠውረዋል ፤ ከተሠወሩትም ደጋግ ሰዎች አንዱ ሄኖክ ነው ። ይህንንም ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ ሄኖክ ሞትን እንዳያይ በእምነቱ ተወሰደ እግዚአብሔርም ስለወሰደው አልተገኘም ሳይወሰድ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና" ብሏል ዕብ፡፲፩፡፭

እግዚአብሔር ኤልያስን ከእነሥጋው ወደ ሰማይ ለማሳረግ በፈቀደ ጊዜ ኤልያስና ኤልሳዕ ከጊልጊል ተነሡ ። ኤልያስ ኤልሳዕን ከዚህ ተቀመጥ እኔን እግዚአብሔር ወደቤቴል ልኮልኛልና አለው ። ኤልሳዕ ግን ኤልያስ እንደሚነጠቅ አውቆ አልለይህም ስላለው ሁለቱ አብረው ወደ ቤቴል ሄዱ ። በቤቴልም የነበሩ ነቢያት ወደ ኤልሳዕ ቀርበው እግዚአብሔር ዛሬ ኤልያስን ከአንተ ለይቶ እንደሚወስደው ታውቃለህን አሉት ። ኤልሳዕም አዎን አውቃለሁ ዝም በሉ አላቸው ።

ሁለቱ ኤልያስና ኤልሳዕ አብረው ወደ ኢያሪኮ ቀጥሎም ወደ ዮርዳኖስ ሄዱ ። ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ ኤልያስ ኤልሳዕን የምትሻውን ለምነኝ ከአንተ ሳልለይ አደርግልህ ዘንድ ባለው ጊዜ በአንተ ላይ ያደረ መንፈስ በእኔ እጽፍ ድርብ ሆኖ ያድርብኝ ዘንድ እለምንሃለሁ ባለው ጊዜ አስቸጋሪ ነገር ለመንሽ ነገር ግን ከአንተ ስለይ ብታየኝ የለመንከው ይሆንልሃል ያለዚያ ግን ይህ ነገር አይሆንልህም አለው ።

ይህንን ከተነጋገሩ በኋላ እያዘገሙ ሲጓዙ የእሳት ሠረገላ ከእሳት ፈረስ ጋር መጣና ከመካከላቸው በመቆም ለያቸው ኤልያስም በአውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ወጣ ፪ኛ ፡ ነገ፡፪፡፲፩

ከዚህ ላይ የተጠቀሱት ከልደተ ክርስቶስ በፊት የተፈጸሙ ታሪኮች ናቸው ። ወደ ዘመነ ሐዲስም መለስ ብለን ስንመለከት በሕይወተ ሥጋ እንዳሉ የተሠወሩ የእግዚአብሔር ወዳጆችን እናገኛለን ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር ከእነዚህ ከቆሙት ሞትን የማይቀምሱ አሉ ብሎ እንደተናገረው እርሱ ሲያስተምራቸው ከነበሩት ደቀ መዛሙርት ሐዋርያው ዮሐንስ በአካለ ሥጋ እንደተሠወረ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል ። እንዲሁም "እነ አቡነ አረጋዊና የመሳሰሉትም ደጋግ ሰዎች ከእነ ሥጋቸው የተሠወሩ መሆናቸው የታወቀ ነው ። ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ በብሉይ ሥጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት አይችሉም ።

ይህንንም ሐዋርያው ጳውሎስ ሲያስተምር "በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነው እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ



እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉትን አንቀድምም ጌታ ራሱ በትዕዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳል በክርስቶስም አምነው የሞቱ አስቀድሞ ይነሣሉ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ" ብሏል ፩ኛ ተሰ፡፬ ፡ ፲፭—፲፰

ሐዋርያው እንደተናገረው በክርስቶስ ስም አምነን የምንኖር አማንያን ሁሉ ብንኖርም ብንሞትም በክርስቶስ ስለሆነ በዚህ ቃል መጽናናት ይኖርብናል በግዘፈ ሥጋ እንዳሉ የተሠወሩትም በሕይወተ ሥጋ በዚህ ዓለም ያሉትም የሞቱትም ሁሉ አንድ ሆነው የሚነሡበት ጊዜ እንዳለ የታወቀ ነው ። በዚያን ጊዜም ለሁሉ እንደሥራው ዋጋውን ይሰጠዋል ።

በዚህ አንፃር ለማሳሰብ የምንፈልገው ስለሙታን መቃብር ነው ። የሙታን አስከሬን ማሳረፊያ ቦታ አዘጋጅታ የምታስተናግደው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መሆኗ የታወቀ ነው ይህም የሚያስረዳው ቤተ ክርስቲያኖቻችን ለሞቱት ለነፍሳቸው በሕይወተ ሥጋ ላሉት ለሕይወተ ሥጋቸው መማፀኛ መሆኗን ነው ።

በአሁኑ ጊዜ በዋና ዋና ከተሞች የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የተወሰነላቸው ክልል ለመቃብር እየጠበበ አንዳንድ ችግር እየተፈጠረ መሆኑ አያጠያይቅም ። በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ችግሩ እየባሰ መጥቷል ። ትንሽ የቆየውን አስከሬን አውጥቶ ከዚያው ጋር ትኩሱን እሬሳ መቀበር የአደባባይ ምሥጢር ሆኗል ። ይህንን ችግር ካህናትም ምእመናንም በቸልታ መመልከት አይኖርባቸውም ። በአንድ ቦታ ብዙ አስከሬን የሚያርፍበት ዘዴ መፈለግ አለበት ። ርቀን ሳንሄድ ከአዲስ አበባ ከተማ ፩፻፴ ኪ.ሜ. ርቆ ሚገኘው ደብረ ብርሃን ሥላሴ ተጀምሮ ይሠራበታል ። ያንን አጥንቶ በሥራ ላይ እንዲውል ቢደረግ የመቃብር ጥበት ላለባቸው አብያተ ክርስቲያናት ዋና መፍትሔ ይሆን ይመስለናል ።

ይህ ካልሆነ ደግሞ ከተማ ዳርቻ የታነፁ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ ያለውን ቦታ ሰፋ አድርጎ ይዞ በከተማ የሚኖሩት ምእመናን አስከሬን በዚያ እንዲያርፍ ቢደረግ ችግሩ ይወገዳል ብለን እናምናለን ።

ይህንን ስናሳስብ የመእመናን አስከሬን በሚኖሩበት ቤተ ክርስቲያን አካባቢ አይረፍ ማለታችን እንዳልሆነ ምእመናን ሊገነዘቡት ይገባል ። ከላይ እንደተናገርነው የአስከሬን ማስቀመጫ ቦታ ከተዘጋጀ ችግር አይኖርም ነገር ግን አስከሬኑን አውጥቶ ሌላ አስከሬን ደርቦ መቀበሩ ታላቅ ስሕተት ነውና ይታሰብበት እንላለን ።

ለተከበራችሁ አንባብያን ለማሳሰብ የምንፈልገው የክርስቲያኖች ሥጋ የትም ቦታ ቢወድቅ ክብር ያለው መሆኑን ነው ። በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ቢቀበርም ፤ በጫካ ተጥሎ ቢቀርም የሙታን ነፍሶቻቸው የሚድኑት በሃይማኖታቸው ጽናት በመልካም ምግባራቸው እንጂ በመቃብራቸው ማማር አይደለም ። በመቃብር ማማር ክብር እንደማይገኝ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን የነቢያትን መቃብር ስለምትሠሩ የጻድቃንንም መቃብር ስለምታስጌጡ ወዮላችሁ ! ብሏል ማቴ ፳፫ ፳፱ ዳዊት ይህንን ሲያስረዳ ። ወሥጋሆሙ ለጻድቃኒከ ለአራዊተ ገዳም የደጋግ ሰዎች ሥጋቸው የዱር አራዊት ምግብ ነው ብሏል ።

ስለዚህ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገቡት በዓፀደ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ በክብር የተቀበሩት ብቻ አይደሉም በዱር በገደል ወድቀው ሥጋቸውን አውሬ የበላው ነፋስ የበተነው አሞራ የገተነው ቢሆንም በእግዚአብሔር ስም አምኖ የተጠመቀ ከሆነ ወደ መንግሥተ ሰማያት የመግባት ተስፋ አለው ።

ለዚህ ሁሉ ተዘጋጅቶ መኖር አስፈላጊ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል ። ዝግጅትም ሲባል በአንድ አቅጣጫ የሚፈጸም አይደለም ። ለሥጋም ለነፍስም የሚጠቅም ዝግጅት ማድረግ ተፈላጊ ነው ።

የምንሠራው ሥራ ሁሉ ለተከታይ ትውልድ በመልካም ምሳሌነት የሚጠቀስ መሆን አለበት ። ከላይ እንደጠቀስናቸው አበው ያለየ እውነት ሥራ ሠርቶ ስምን በታሪክ ማስመዝገብ ከእያንዳንዱ ምእመን ይጠበቃል ።

ስማቸው በታሪክ መዝገብ የተመዘገቡት ሰዎች ሁሉ ከእኛ የተለየ ተፈጥሮ የላቸውም ። ሁሉም እንደኛ ሰዎች ነበሩ ፤ ነገር ግን በመልካም ሥራቸው ለሌሎች ማስተማሪያ ለመሆን በቅተዋል ።

ስለዚህ ማሰብ ያለብን የዕለቱን ብቻ አይደለም ። ለራሳችንም ሆነ ለወገኖቻችን አርቆ የማስብና የማስተዋል ስሜት ሊኖረን ይገባል — ሞኝ የዕለቱን ብልህ የዓመቱን ተብሎ በመነሻው እንደተጠቀሰው እንደሞኝ ጊዜያዊውን ተግባር ብቻ ሳይሆን እንደብልህ ለሁልጊዜ ቀዋሚ የሆነውን ሥራ ለመሥራት መዘጋጀት ይኖርብናል ።



www.ethiopianorthodox.org

# መንፈሳዊ ሹመት
# የመምህር ተክለማርያም ዓምደጊዮርጊስ
# የሕይወት ታሪክ

መምህር ተክለ ማርያም በኤርትራ ክፍለ ሀገር (ሰንጊት) ክረን አውራጃ ልዩ ስሙ አድርባ ሚካኤል በተባለው ቀበሌ ከአባታቸው ከአቶ ዓምደ ጊዮርጊስ ዕቁበ ጽዮን ከእናታቸው ከወይዘሮ ወለተ ቅዱሳን ዓምደሚካኤል በ፲፱፻፲፯ ዓ.ም ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በጸዕዳ ዓምባ ሥላሴ ገዳም ንባብና ዳዊት ከቃል ትምህርት ጋር አጠናቀው ተማሩ ከዚያም ቀጥለው ሰዓታትንና ግብረ ዲቁናን አውቀው ለማዕረግ ዲቁና የሚያበቃውን ትምህርት ከተማሩ በኋላ በዘመኑ የኤርትራ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ ማዕረገ ዲቁና ተቀብለው በተወለዱበት ቀበሌ በቅዳሴና በሰዓታት መንፈሳዊ ተልዕኮዋቸውን ሲፈጽሙ ከቆዩ በኋላ በሠራዬ አውራጃ ወደ ሚገኘውና ደብረ ድኁሃን በመባል ወደ ታወቀው ታላቁ የአቡነ ዮናስ ገዳም ገብተው ግብረ ክህነትን እየተማሩ በገዳሙ የሚገኙትን አረጋውያን እየረዱ ከፍ ያለ ትሩፋትንና መንፈሳዊ አገልግሎትን አበርክተዋል።



ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ የሢመት ልብሳቸውን እንደለበሱ

መምህር ተክለ ማርያም በገዳሙ የሚፈጽሙትን መንፈሳዊ ተልዕኮ በመመልከት በገዳሙ መነኮሳት ታላቅ ተወዳጅነት አትርፈዋል ። የመምህር ተክለ ማርያም ዓምደ ጊዮርጊስ ሐሳብ ከሴትርቀ ንጽሕናን ጠብቆ መኖር ስለነበርና በአርዐተ ምንኩስና ተጠምደው መኖር በመሆኑ በደብረ ድኁሃን ገዳም አርዐተ ምንኩስና ተቀበሉ ።

መምህር ተክለ ማርያም ከመንኮሳቸው አስቀድመው ጸዋትወ ዜማን ከመማራቸውም በላይ አቋቋም ቅኔ የመሳሰሉትንና በበለጠ ደግሞ መዝገበ ቅዳሴን ለመምህርነት በሚያበቃ ሁኔታ በመማራቸው በመምህርነት ተመርቀዋል ። በዚህም መሠረት በገዳሙ ውስጥ ለ10 ዓመት ያህል ወምበር ዘርግተው ብዙ ደቀ መዛሙርትን ለቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ቁም ጽፈትም በሚገባ አጠናቀው ያውቃሉ ።



መምህር ተክለ ማርያም በዚህ እንዳሉ ማዕረገ ቅስና ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ በ፲፱፻፴፰ ዓ.ም ተቀብለዋል እንደዚሁም ማዕረገ ቁምስናን ከብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ተቀብለዋል ።

ይህ ብቻ አይደለም ከቅዳሴ መምህርነታቸውም በኋላ ግብረ ገብነታቸውን በመመልከት በአበው መነኮሳት ተመርጠው ፬ ዓመት ያህል ገዳሙን በአስተዳዳሪነት አገልግለዋል ።

መምህር ተክለ ማርያም ዓምደ ጊዮርጊስ በኤርትራ ሀ ስብከት በዋና ጸሐፊነትና በመንፈሳዊ ዳኝነት ከማገልገላቸውም ሌላ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተዘዋወሩ ወንጌልን ማስተማር ደግሞ ዕለታዊ ተግባራቸው ነው ። እንደዚሁም በአሥመራ ከተማ ለተሠራው የስብከተ ወንጌል ሕንፃ ማሠሪያ የገንዘብ መዋጮ ሲደረግ በየአውራጃው እየተገኙ ሕዝቡን በማስተማርና በማበረታታት የደከሙት ድካም በቀላሉ የሚገመት አይደለም ።

በክፍለ ሀገሩ ለደረሰውም ችግር ለሰላም ጥረት መፍትሔ ለመፈለግ የሰላም ጉባኤ ሲቋቋም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በመወከልና አባል በመሆን ከፍተኛ ድርሻ አበርክተዋል ።


መምህር ተክለ ማርያም የፈጸሙት መንፈሳዊ ተልዕኮ በዚሁ ሳይወሰን በሕፃናት ማሳደጊያ ፍኖተ ብርሃንና በመሠረተ ትምህርትም በኩል የከፈሉት የሥራ አስተዋጽኦ እጅግ የላቀ ሁኖ በመገኘቱ ከሁሉቱም ድርጅቶች የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ። ቤተ ክርስቲያንን ለማስፋፋት ሃይማኖትንም ለማጽናት በሚደረገው መንፈሳዊ ጉባኤም በኤርትራ ሀገረ ስብከት በሚገኙት አውራጃዎች ከሀገረ ስብከቱ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድረስ በመዘዋወረ ሰበካ ጉባዔን በማቋቋምና በማጠናከር የሰንበት ተማሮችን በማሰባሰብና በማስተማር ያደረጉት ጥረት ወሰን የለውም ።

ይህንንም መንፈሳዊ ተልዕኮዋቸውን ያጠና ቅዱስ ሲኖዶስና የመምህር ተክለ ማርያም መንፈሳዊ ሥራ አመራርን የተገነዘቡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያም መልክም ፈቃዳቸው ሁኖ ለዚህ ከፍተኛ ሹመት አብቅተቸዋል ።

## የሲመቱ አፈጻጸም

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ተክለ ሃይማኖት ከሊቃነ ጳጳሳቱ ጋር በዓውደ ምሕረት ወደ ተዘጋጀው መንበረ ክብር ወጥተው እንደተቀመጡ ከየአድባራቱ የመጡ መዘምራን በዓውደ ምሕረቱ ለ፲፰ ደቂቃ ያህል ካሸበሸቡ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቃለ ምዕዳን ሰጥተው በቡራኬ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

ከንፈርግብ " ርቆስ



ብፁዕነታቸው ስለተጣለባቸው ሐላፊነት ያስባሉ



www.ethiopianorthodox.org

# ዋና ሥራ አስኪያጁ በወሎ የሕፃናት ማሳደጊያዎችን ጐበኙ

ሊቀ ማዕምራን ደምፀ ገብረ መድኅን የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ የቦርድ ሊቀ መንበር ከሚያዝያ ፳፬ ቀን እስከ ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹ ዓ. ም ድረስ በወሎ ክፍለ ሀገር የሚገኙትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት ማሳደጊያዎች ተዘዋውረው ጐብኝተዋል ።

ስለዚሁ የዋና ሥራ አስኪያጅ የሥራ ጉብኝት ከሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ጽ/ቤት በወጣው መርሐ ግብር መሠረት ዋና ሥራ አስኪያጁ በኮምቦልቻ ፡ በደሴ ከተማና በወልድያ ከተማ የሚገኙትን የሕፃናት ማሳደጊያዎች አንድ በአንድ ተዘዋውረው በመጐብኘት ለየአዳሪ ቤቶቹ ዲሬክተሮችና ሠራተኞች የሥራ መመሪያ ለሕፃናቱም የማበረታቻ ምክርና የሞራል ድጋፍ ሰጥተዋል ።

ዋና ሥራ አስኪያጁ በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በደሴ ዙሪያ አውራጃ በቁንዲና በገራዶ እንዲሁም በቃሉ አውራጃ በሀርቡ በድርቅ ጉዳት የደረሰባቸውን ፶፻፺ ችግረኞችን ለመርዳት ያቋቋመቻቸውን የዕርዳታ መስጫ ጣቢያዎችን ተዘዋውረው ከጐበኙ በኋላ ርዳታ የመስጠቱ መርሐ ግብር ስለሚፋጠንበት ሁኔታና ስለዘለቄታው የመልሶ ማቋቋም ፕሮግራም ለየጣቢያው ኃላፊዎችና ሠራተኞች አስፈላጊውን የሥራ መመሪያና ምክር ለግሰው ተመልሰዋል ።

# ሥራ ሕይወት ነው

ሥራ ሕይወት መሆኑን ከተረዳን ሕይወትም ሥራ መሆኑን ማወቁ አይሳነንም ለምሳሌ ህንፃ ያለ መሠረት ጣሪም ያለ ቋሚ እንደማይጸና ሁሉ ሕይወትም ያለ ሥራ ሥራም ያለ ሕይወት ሊቋቋም አይችልም ምክንያቱም ሥራ ባስገኘው በእህልና በውኃ ሕየወት ካልተደገፈ ሕይወትም ኃይል አግኝቶ ካልሠራ እነዚህ ሁለቱ ካልተደጋገፉ ሁሉ ነገር ተሟልቶ ሊካሄድ ስለማይቻል ነው ። ይህም ቢሆን ለመብላት መኖር ሳይሆን ለመኖር መብላትና መሥራት የሚለውን ዘይቤ መከተል ያስፈልጋል።

ይኸውም እግዚአብሔር አምላክ በዘፍጥረት ላይ ለአዳም የሰጠው ትእዛዝ ሠርቶ የሥራውን ፍሬ እንዲበላ ነው ። እግዚአብሔር አምላክ ይህ ትእዛዝ ለሌሎችም ጥሩ ምሳሌና አርአያ እንዲሆን የሥራ ክቡርነትና ሕይወት መሆኑን ከማሳየቱም ሌላ የሥራ ትንሽና ትልቅ እንደ ሌለውም እየሠራ አሳይቶዋል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከገበሬዎችና ከሠራተኞች ጋር ጐን ለጐን ሲሄድ ሳለ በሰዎች ዘንድ ሳይታወቅና ሳይከበር መላእክትን ያገለግሉት ነበር ። እርሱ በነበረበት ዘመን እንዳሁኑ ጊዜ የእንጨት መሰንጠቂያ ባለመኖሩ ሁሉ ነገር የሚሠራው በእጅ ስለነበር ለመስኮትና ለበር መዝጊያ የሚሆኑትን ሳንቃዎች እየጠረበና እየላገ ሠርቶ ይገጥም ነበር ። በዚህም በኩል በዚያን ዘመን ይኖር ለነበረው ህብረተሰብ ታላቅ አገልግሎት ሊሰጥ ከመቻሉም ሌላ በሥራው ብዙ ሰዎች ይደነቁበት እንደነበር ከተአምረ ኢየሱስ እናገኛለን በጥበብና ሞገስ በመንፈስም እያደገ ከመሄዱም ሌላ ለዘመዶቹም ይታዘዛቸው እንደነበረ ሉቃስ ጽፎአል ሉቃስ ምዕራፍ ፪ ቁጥር ፶፩

ሥራ ሕይወት ነው ሕይወት ሥራ ነው በሚለው መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም የህይወት ብርሃን ፡ የደስታ ምንጭ እንደመሆኑ መጠን የብርሃን ጸዳል እንደሚወጣ ሙቀት ከውኃም ህይወት ካለው ምንጭ ፈልቆ እንደሚወርድ ፈሳሽ ምህረት ጠንነትና በረከት ከእርሱ ዘንድ ወጥቶ ለፍጥረት ሁሉ ይጎርፋል የተለያየውን እንጨት ገጥሞና አንድ አድርጎ ውበት እንደሚሰጠው ሁሉ በልዩ ልዩ ቁስልና ደዌ ተነካክቶና ተሰባጥሮ ተለያይቶ የነበረውን የሰዎችን አካል አድኖ ህይወት ከመስጠቱም ሌላ እጃቸው የሰለለውን እግራቸው ያነከሰውንና ጆርባቸው የጎበጠውን ሀሙማን ሐይል አግኝተው እራሳቸውን በራሳቸው እየረዱ የህብረተሰቡ ሸክም እንዳይሆኑ ውበትና መልክ ሰጥቶአቸዋል ።

በጠቅላላው የታመሙትን እየፈወሰ አውሎ ነፋስ በሚያናውጸው በገሊላ ባህር ላይ እየተመላለሰና በትህትና እየሠራ መልእክቱን የታመነ ሆኖ ፈጽሚል እንዲሁ በትሁት ሥራ በተዋረደ ኑሮ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ልንመሳሰልና ልንሠራ ይገባናል። ሥራ ወዳድ የሆነው ቅዱስ ጳውሎስም "ወንድሞቼ ሆይ እያንዳንዱ በእግዚአብሔር ዘንድ በተጠራበት ይኑር" ብሏል አንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ፯ ቁጥር ፳፬ ሠራተኛ ሰው የታመነ ስለሆነ ጌታው በሚመሰገንበት መንገድ በሥራው ፊት ፊት እየመራ ይሄዳል ። እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ ከሆነ በሚያደርገው ነገር ሁሉ እምነትና ምግባር ያሳያል ። የክርስቶስ ንም ሥራ ለሰዎች ይገልጻል ይኸውም መንገደኛ ተራራውን ዝቅ በማድረግና ሸለቆውን በመሙላት በሠራው በኢየሱስ ፊት የተጋና የታመነ መንገደኛ ይሆናል የክርስቶስንም ስም የሚጠራ ሁሉ እንዲሁ ሊሠራ ይገባዋል ።

ይህ ከሆነ በጸጋ የምናድገበት መንገድ የራሳችንን ጥቅም ብቻ ሳንፈልግ ክርስቶስ በኛ ላይ የጣለውን ሥራ መሥራት ነው ሥራውን ለመዘርጋት እንደሚቻለን መጠን የኛን እርዳታ ለሚፈልጉት መርዳት ይገባናል ። ኃይልና የሥራ ልምድ አዘውትሮ ከመሥራት ይገኛል ሥራ ለህይወት ዋና ድጋፍ ስለሆነ ሁላችንም መሥራት ያስፈልገናል ይሁን እንጂ ለክርስቶስ አንዳች ሥራ ሳይሠሩ ከጸጋው የሚመጣውን በረከት በመቀበል የክርስቶስን ህይወት ለማግኘት የሚጥሩ ሳይደክሙና ሳይሠሩ መብላትን የሚፈልጉ እራሳቸውንም እየፈተኑ ሌላውንም የሚፈትኑ አልታጡም ይህም እንግዳ ነገር ሳይሆን በዓለም እንደ ሚደረገው ሁሉ በመንፈሳዊም በኩል አንዳንድ ጊዜ ስለሚደረግ ውርደትና ጥፋት ያመጣል የፍጥረትንም ባህርይ ይለውጣል ማንኛውም ሰው ይህን ከፈጸመ አካሉን በሥራ ካላለማመደ በቶሎ ኃይል ያጣል ።

ቤተ ክርስቲያንም ሰውን ለማዳንና የሥራ ልምምድ አድርጎ የሥራ ፍቅር እንዲኖረው ለማድረግ በክርስቶስ ደም የተመሰረተች የሐዋርያት ማህበር ናት የተቋቋመችውም ወንጌልን ለዓለም ለማዳረስ ነው ። ይህም ክርስቲያን ለሆነ ሁሉ የውዴታ ግዴታ ሥራው ነው ። ሁሉም እያንዳንዱ ይህን የህይወት ሥራ ለመፈጸም የተቀበለውን መክሊት ለማብዛትና ይህን የተመቸ ጊዜ በከንቱ አለማሳለፍ ይገባዋል ። ለኛ የተገለጸውን የክርስቶስን ፍቅር እርሱን ለማያውቁ ሰዎች ካልገለጽን ላቸው የኅዘያ ዕዳ ከእኛ ላይ ይሆናል ። አንድ ሊቅ ሲናገር "ሰው ሁሉ የያዘውን ሻማ ቢያበራ ዓለም በሙሉ ብርሃን በሆነ ነበር" ብሏል ። አባባሉ መልካም ነበር ታዲያ ማን ይተባበራል? እኛም ብንሆን ከክርስቶስ የተሰጠን መብራት ለኛ ብቻ አይደለም ፡ ለሌሎችም እንድናበራላቸው ነው።

ይኸውም የክርስቶስን ኃይል ከለበስን በውስጥ የሚደረገው የመንፈስ ደስታም በልባችን ከመላብን ዝም ልንል አንችልም ። ጌታ ለኛ ቸር እንደሆነ ከቀመስንና ካየን የመንሰራው ሥራ አለን በበአሉ እኩሌታ የመጡት የግሪክ ሰዎች ፊልጶስን ከጌታ ጋር እንዲያነጋግራቸው ጠየቁት እሱም አገናኝቶ አነጋገራቸው እኛም ብንሆን እንዲህ ያለውን ሥራ ሠርተን ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ልንስባቸው ይገባል በመሆኑም ክርስቶስን ለማገልገል ሥራችን ባገራችን ቢሆን በዚያው ባገራችን ዙሪያ በቤተ ክርስቲያን አብረናቸው ከምንቀመጠው ሰዎች ጋር አብረናቸው ከምንሠራ ሠራተኞች ጋር ልንፈጽመው ያስፈልገናል ።

ሥራ አበባ ነው ከተሰሙ በኋላ እንደማር አጣፍጦ ሠርቶ ለወገን ለሀገር ለቤተ ክርስቲያን ማቅረብ ይገባል ። ሥራ ህይወት ነው ህይወትም ሥራ ነው ። የሚባለው ይህ ተሟልቶ ሲገኝ ነው ። ይህ ከሆነ ባለንበት ዘመን ሁሉ ሥራችንን በፍቅር መንፈስ ለጌታችን እንሠራለን ይኸውም የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን መኖሩ በሥራችን ይታወቃል ። መንፈስ ቅዱስ በዙሪያችን ሲከበን ሥራችንም ከፍ ያለና የተባረከ ይሆናል ሥራ ህይወት ነውና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

# ዜና ዮሐንስ አፈወርቅ

ዮሐንስ የትውልድ ሀገሩ አንጾኪያ ነው ይህችም አገር በአሁኑ ጊዜ በቱርክ ግዛት ሥር ትገኛለች። የዮሐንስ ወላጅ አባቱ ሴኮንዱስ ሲሆን እናቱ ደግሞ አትናስያ ትባላለች ፡ ከእነኚህ ሰዎችም የተለደበት ዘመን በ፫፻፵፬ ዓ ም ነው ።

የወላጅ አባቱ ሙያው ወትድርና ሲሆን ሥራውም የወታደሮች አለቃ ነበር ፡ በወታደር ሠራተኞችም ዘንድ እጅግ በጣም ሲበዛ ተወዳጅነት ነበረው ፡ ነገር ግን ዮሐንስ ልጁን አስተምሮና አሳድጎ ለቁም ነገር ማብቃት አልቻለም ፡ ምክንያቱም ዮሐንስ እንደ ተወለደ ወዲያውኑ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል ፡ ወላጅ እናቱ ግን ሃያ ዓመት እስኪሞላው ድረስ እያስተማረች በሚገባ አሳድጋዋለች ።

ዮሐንስ ትምህርቱን የተማረውም ለመጀመሪያ ጊዜ እናቱ ወስዳ በሰጠችው ሊባንዮ ከሚባል አስተማሪ ነው ፡ ይህም መምህር በዚያን ጊዜ ከነበሩት መምህራን መካከል ከፍተኛ ዝና የነበረውና እጅግ በጣም ተወዳጅነት ያለው ነበር ። መምህሩም ትምህርቱን በሚገባ አስተምሮታል ። ዮሐንስ ይህ ብቻ ሳይሆን ከሌላም አስተማሪ የፍልስፍናንና የሕግ ትምህርት በሚገባ ተምሯል ።

ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርቱን

(ወደ ገጽ ፲፮ ይዞራል)





www.ethiopianorthodox.org

# «ማስተማር አምላካዊ ትእዛዝ ነው»

መነሻውም "ሑሩ ወመሐሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም" ወደ ዓለም ዳርቻ ሂዱችሁ አስተምሩ የሚለው ነው ። በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ማስተማር ከእግዚአብሔር የታዘዘ መንፈሳዊ ሕግ ሲሆን ተምሮ አለማስተማር ደግሞ ከፈጣሪ ከፍተኛ ወቀሳን የሚያስከትል ፡ ውሎ አድሮም ቅጣትን የሚያመጣ ነው ።

ሰበካ ጉባኤን ለማቋቋምና ፡ ምእመናንም በሃይማኖትና በሥነ ምግባር እንዲጸኑ ለማድረግ ፡ የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን አንድነት እንዲጠነክር ፡ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት የተሟላ እንዲሆን ፡ የአገልጋዮች ካህናት ኑሮ የዘለቄታ ዋስትና እን ዲኖረው ከሁሉ በፊት የስብከተ ወንጌል መጠናከርና መስፋፋት አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው።

ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለዓለም የምታበስረውና የምታስተዋውቀው ፡ ዓለም በንስሐ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርብ ፡ በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍን የምታውጀው በትምህርተ ወንጌል ስለሆነ ነው ።

በትንቢተ ኢሳይያስ እንደምናነበው ልዑል "እግዚአብሔር" ወደ ሕዝቡ ማንን እልከዋለሁ? ማንስ ይላክልኛል?" ያለበት ወቅት እንደነበረ ስናስታውስ ለዚህ ጥሪ የታደለው ነቢዩ ኢሳይያስ እኔ እላክ ነበር ፡ ዳሩ ግን ለምጻም ነኝ ብሎ ራሱን በግልፅ አቀረበ እግዚአብሔርም የነቢዩን በጐ ፈቃድ አውቆ ከሱራፌል አንዱ የእሳት ጉጠት ይዞ ከለምፁ እንዲያነፃው ከአደረገ በኋላ ወዲያውኑ ሕዝቡን እንዲያስተምር እን ደላከው እንገነዘባለን ። ትን.ኢሳ ፮·፰

በዚህ ዓይነት ቀደም ሲል ነቢያት ፡ ከዚያም ሐዋርያት ፡ በኋላም ሊቃውንት እየተላኩ ሕዝቡን ሲያስተምሩ ፡ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሲያቀርቡና ሲያዘጋጁ ኑረዋል ።

ለዚህ የተቀደሰ አገልግሎት ድኅረ ልደት ብቻ ሳይሆን ቅድመ ልደትም ሳይቀር ሰዎችን ከማሕፀን ጀምሮ ይመርጥና ያዘጋጅ እን ደነበር ከቅዱሳት መጻሕፍት እንረ ዳለን ።

መረጃውም፡- "በሆድ ሳለህ አወቅሁህ ፡ ከማሕፀንም ሳትወጣ ቀደስሁህ ፡ ለአሕዛብም ነቢይና መምህር አደረግሁህ" ተብሎ ለነ ቢዩ ኤርምያስ የተነገረውና እንዲ ሁም "ከእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ይሆናል ፡ የወይን ጠጅም አይጠጣም ፡ መንፈስ ቅዱስም በእናቱ ማህፀን ሳለ ጀምሮ ይደርበ ታል ፡ ከእስራኤልም ልጆች ብዙ ዎችን ወደ እግዚአብሔር ወደ አምላካቸው ይመልሳል" ተበሎ ለመጥምቀ መለኮት ዮሐንስ የተነ ገረው ነው ።

በዚህ ዓይነት ልዑል እግዚአብ ሔር በማይታወቅ ጥበቡ ሠራተኞ ቹን በየጊዜውና በየዘመኑ ሲያዘ ጋጅ ኖሮአል ወደፊትም እስከ ዓለም መጨረሻ ያዘጋጃል ።

ክርስቶስ ሐዋያርያትን መርጦ አዘጋጅቶ ወደ ዓለም የላካቸው ምስክሮች እንዲሆኑት ነው ። የሐ.፩.፰

ዓለም በእውነት እንዲጸናና ከሚደርስበትም ሃይማኖታዊና ሥነ ምግባራዊ ፈተና እንዲድን ጽድቅን እንዲያውቅ ፡ እስተዋይ እንዲሆንም ነው ።

ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ከመ ዝ መሀር ወገሥጽ ፡ ወአልቦ ዘያስተአብዳ ለውርዙትከ ወኩኖሙ አርአያ ለመሃይምናን በቃልከ ወበምግባሪከ በፍቅር ወበ ሃይማኖት በንጽሕ በአንብቦ ወበምሂር" (፩ ጢሞ.፬ ፲፪) ሲል እንዳስተማረው ሰባኪ ወን ጌሉ ትምህርተ ወንጌሉን የሚያስ ተላልፈው ሰሚዎች እሱን እንዲ ከተሉና እንዲመስሉ ስለሆነ በሰ ሚዎቹ ዘንድ የሰባኪ ወንጌሉ ሕይወት ግልፅ መሆን ይኖርበ ታል ። ምክንያቱም እርሱ የሚሠ ራውን አትሥሩ ፡ እርሱ የማይሠ ራውን ሥሩ ብሎ የሚያስተምር ከሆነ ትምህርቱ ተቀባይነት አያ ኖረውምና ነው ።

አትስረቁ ብሎ የሚያስተምር መስረቅ ፡ አትሰስኑ ብሎ የሚያስ ተምር መሰሰን ፡ አትዋሹ ብሎ የሚያስተምር ሐሰት መናገር ፡ አትስከሩ ብሎ የሚያስተምር መስ ከር ተፋተፋ ብሎ የሚያስተምር ፀረ ሰላም መሆን የለበትምና ነው ይህ ካልሆነ ግን

"ኩሎ ዘመሀሩክሙ ግብሩ ወዕ ቀቡ ወዘከመ ምግባሮሙስ ኢትግ በሩ እስመ እሙንቱ ዘይሜ ሀሩ ኢይገብሩ ያስተማሯችሁን አድ ርጉ ሥራቸውን ግን አትሥሩ የሚ ያስተምሩትን አያደርጉትምና ተብሎ የተነገረው በመምህሩ ላይ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ነው ።

ሰባኪ ወንጌሉ የሚያስተም



ረው ትምህርት እንዳይናቅና ተተ ባይ እንዳያጣ ፡ እግዚአብሔርን እንዳያስድብ በግል ሕይወቱ ጠን ቃቃ መሆን ይኖርበታል ። ስለ ዚህ ጉዳይ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው የመጀመ ሪያ መልዕክቱ ምዕ.፱.፳፯" .ለሌ ሎች ከአስተማርኩ በኋላ ራሴ የተጣልሁ ሥጋዬን እየጐሰምሁ አስገዛዋለሁ ።" ይላል

ሰባኪ ወንጌሉ ሰሚዎቹ ወይም ተከታዮቹ እሱን እንዲመስሉ ስለ ሆነ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶ ስን እንደመሰልኩት እናንተም እኔን ምሰሉ እንዳለው (፲፩.፩)

ምክንያቱም በክርስትና ትምህ ርት አስመስሎ መናገር ብቻ ሳይ ሆን አስመስሎ መሥራት የሚመ ስሉትን ሆኖ መገኘት ግዴታ ነው።

ይህ ከሆነ "እንትሙ ውእቱ ጼው ለምድር ፡ አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም ፡ ከማሁ ይብራህ ብርሃንክሙ በቅድመ ሰብእ ከመ ይርአዩ ምግባሪክሙ ሠናየ ወይሰ ብሕዎ ለአቡክሙ ዘበሰማያት" ተብሎ ለሐዋርያት የተነገረው ቃለ በረከት በሱ ላይም ተፈጻሚ ነት ሊኖረው ይችላል ።

"ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር" ብሎ የሚያስተምረው ሐዋርያ በእግዚአብሔርና በምዕመናን ያለ አገናኝ ወይም አስተርጓሚ ስለሆነ በትምህርተ ወንጌል የታነፀ ፡ በሥነ ምግባር የተጌጠ ፡ በመን ፈስ ቅዱስ የተቃኘ ፡ ለትምህርተ ወንጌል የነቃ የበቃ መሆን ይኖር በታል ።

ይህ ከሆነ "ለአገልግሎቱ ታማኝ አድርጐ ስለቆጠረኝ ኃይል የሠጠኝን ክርስቶስ ኢየሱ ስን አመሰግናለሁ" ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ጢሞቴዎስ በጻፈው የመጀመሪያ መልእክቱ ምዕ.፩. ፲፪.፲፫. እንደተናገረው ሰባኪ ወን ጌሉም በዚህ ቃል ተጠቃሚ ይሆ ናል ማለት ነው ።

እንግዲህ ስብከተ ወንጌል እን ዲስፋፋ ፡ ሰበካ ጉባኤ እንዲጠና ከር ፡ ትምህርተ ወንጌል በምዕመ ናን ልቡና ተዘርቶ አብቦና አፍርቶ ፍሬ እንዲሠጥ ከተፈለገ ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈስ ቅዱስ ልጁ ለጢሞቴዎስ

እንዳስተማረው ሰባኪ ወንጌሉ የማይነቀፍ ፡ ልከኛ ፡ ራሱን የሚ ገዛ ፡ እንደሚገባው የሚሠራ ፡ እንግዳ ተቀባይ ፡ ለማስተማር የሚተጋና የሚበቃ ፡ የማይሰክር ፡ የማይጨቃጨቅ ገር ፡ በማይረባ ነገር የማይከራከር ገንዘብን እጥ ብቆ የማይወድ ልጆቹን በሥነ ሥርዓት የሚያሳድግ ፡ ቤቱን በመ ልካም የሚያስተዳድር እውነተኛ ሐዋርያ መሆን ይኖርበታል ። (፩ኛ·ጢሞ·፫·፩ ፯)

በመቅድመ ትምህርቱ "እንግ ዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተ ምሩ ፡ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስምም አጥምቁአቸው ፡ እነርሱም ያዘዝኋችሁን ሁሉ እን ዲጠብቁ አስተምሯቸው ፡ እኔም በዘመኑ ሁሉ እስከፍጻሜ ድረስ ከላንት ጋር እሆናለሁ "በሚል የተሠጠውን ትዕዛዝ በማክበር ከዘመድና ከአዝማድ ተለይተው የእግዚአብሔርን ቃል ስንቅ ይዘው ባሕሩን በመርከብ የብሱን በእግር በመሄድ የወንጌልን ቃል ጽንፍ እስከ ጽንፍ ለማዳረስ የበ ቁት ሐዋርያት ንኡዳን ክቡራን ናቸው ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አሠረ ሐዋርያትን ተከትለው ትምህርተ ወንጌልን የሚሰብኩና የሚያስተምሩ የወቅቱ ሐዋርያትም ሊመሰገኑ ይገባል ። ምክንያ ቱም"

"የመልካም ዜና አብሳሪዎች መምጣት በጣም አስደሳች ነው" ተብሎ ተጽፎአልና ስለዚህ እም ነት የሚገባው በማስተምር ነው ማስተማርም አምላካዊ ትእዛዝ ነውና ነቅተንና ተግተን እናስተ ምር ።

ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ አማኑ ኤል

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

## ገዳመ አስቴጥስ ፡

በዛሬው ልማት በቤተ ክርስቲ ያን ዓምዳችን የምንገልፀው ስለ ገዳመ አስቴጥስ ይሆናል ። ገዳመ አስቴጥስ የሚገኘው በጐጃም ሀ ስብከት ከደብረ ማርቆስ ከተማ ፳ ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ነው ።

ይህ ገዳም የተመሠረተው በ፲፱፻፸፪ ዓ ም ሲሆን የመሠረቱ ትም የጐጃም ሀ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ናቸው ። ብፁዕነታቸው ገዳሙን ሲመሠርቱ ለትምህርተ ሃይማ ኖት ለልማት በጽሙና ለመጸለይ የሚቻልበት ቦታ መሆኑን ተገንዝ በው እንደሆነ የታመነ ነው ። ገዳሙ በተመሠረተ በሁለተኛው ዓመት በ፲፱፻፸፫ ዓ ም ብፁዕ ወቅ ዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትር ያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮ ጵያ ቦታውን ጐብኝተው ባርከው ይህ ቦታ ለትምህርትም ለጸሎ ትም ለልማትም አመቺ ነው በዚህ የፈለቀውም ፀበል የሕሙ ማን መፈወሻ ይሆናል ብለው ፡



www.ethiopianorthodox.org

ዐበሉ ከሚፈልቅበት ላይ ጸሉተ ኪዳን አድርሰው ቡራኬ ሰጥተው በት ነበር ፡ በዚያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑ በሚገባ እንደዛሬው ስላልተሠራ ታቦቱ በመቃኛ ነበር የሚቀድሱትም ካህናት የሚመጡት ደብረ ማርቆስ በመንበረ ጽጽስናው የሚኖሩ መነኮሳት ነበሩ ። ገዳመ አስቄጥስ ብለው የሰየሙትም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያንጊዜ ገዳሙን ሲጎበኙ ነው ።

ገዳሙ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በብፁዕ አቡነ መቃርዮስ አመራር ያደረገው እርምጃ እጅግ በጣም የሚያስደንቅና የሚያስገርም ነው፡ ያን ጊዜ ለዓይን ማረፊያ አንድ እንጨት ያልነበረው በታ

አሁን በልዩ ልዩ ዛፍና ተክል አበባና ለምለሚ አጊጦ ይታያል ። ያንጊዜ ከትንሽ መቃረቢያ በስተቀር ሌላ ያልነበረው ቤተ ክርስቲያን በዘመናዊ ፎርም ከመታነጹም ሌላ ግድግዳውም ጠፈሩም በሥዕል አሸብርቆ ይገኛል ። ከዚሁም ጋር በገዳሙ ለሚኖሩ መናንያን መምህራንና ተማሮች መኖሪያ ብዙ ቤቶችና ጉጆዎች ተሥርተዋል ፡ ከዚህ ላይ ቤት ያልናቸው ታላላቆችን ሲሆን ጎጆዎች ያልናቸው ደግሞ የቅኔ ተማሮች የሚኖሩባቸውን ነው ።

በልማትም በኩል ከላይ እንደገለጽነው ብዙ ባህር ዛፎችን ድከራን የሚባሉ አትክልቶች ተተክለው የገዳሙን ቦታ ሸፍነውታል ፡ በዚህ ዓመትም የሚተከሉት ችግኞች ፈልተው ጉድጓዳቸው ተምሶ ወቅቱን በመጠበቅ ላይ ይገኛሉ ። የአትክልት ኃላፊ የሆኑትን አባ ወልደ ገብርኤል ብርሃኑን ጠይቀናቸው ሲያስረዱ በገዳሙ ክልል ውስጥ እንደተመለከታችሁት ብዙ ችግኞች ተተክለው ስለለመዱልን ገዳሙን ደን ለበስ አድርገውታል አሁንም ወደፊትም ሥራችን እያጠናከርን ገዳሙን እያለማን እንረዳለን ፡

ብፁዕ አቡነ ማቃርዮስ የገዳሙን ዕድገት በጢት በማታ ነትተው ስለሚከታተሉ ብየጊዜው ከፍተኛ ዕድገት እያሳየ ነው በዚህ ገዳም ልማቱን በሚገባ የሚከሂዱ የወር ደመወዝ የሚከፈላቸው ፲፫ ሠራተኞች ይገኛሉ ያለፈውን ዓመት ሳንጨምር በዚህ በያዝነው ዓመት ብቻ ፩፻፳ሺ የባሕር ዛፍ ችግኝ አፍልተናል በማለት የፈሉትን ችግኞች ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳትና ለብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፡ እንዲሁም ለቅዱስነታቸው የክብር ተከታዎች አስጎብኝተዋል ፡ ቅዱስነታቸውም በተመለከቱትና በጎበኙት ሁሉ የረኩ መሆናቸውን ለሀ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ገልጸውላቸዋል ። ገዳሙ የአንድነት ገዳም እንደመሆኑ መጠን በመቁንን የሚመገቡ ፹ ገዳማውያን ሰዎች መኖሪያቸው ተገልጿል በገዳሙም የመጽሐፍ ፡ የዐዋትወ ዜማ ፡ የቅኔ የቅዳሴ መምህራን መኖራቸው ታውቋል ፡ ከጉብኝቱ በኋላ ስለቅዱስነታቸው ክብር በገዳሙ ግብዣ ተደርጓል ። ከግብዣውም በኋላ ከሊቃውንትና በገዳሙ ከሚማሩ ተማሮች ብዙ ቅኔዎች ለቅዱስነታቸው ተበርክተዋል ብዙ ግጥሞችም ተነበዋል ፡

በገዳሙ ጉብኝት ጊዜ ለቅዱስነታቸው ከተበረከቱት ቅኔዎች በጥቂቱ ቀጥለን ለአንባብያን አቅርበናል ፡

ሥላሴ ቅኔ ዘመሪጌታ ኀሩይ ዓለማየሁ የዐዋትወ ዜማ መምህር

ይዕቀቡ ፍጥረታተ ተግባራተ ልማት ኪሩቤል ፤ ዐወርተ ፍሬ መንበረ ዘበበገጹ ይሠሩ ።

መቃርዮስ አምጣነ አዘዘ ወእሉ ተፈጥሩ ፡

ወቀዳማዊ መልአክ ተክለ ሃይማኖት ፍቁሩ

በነበ አንጸረ የሐውሩ

ገባዕተ አስቄጥስነት እለ ቄጥሩ

እስመ እሉ በባሕር ኀበሩ

ትርጉሙ ፡

የልማት ሥራዎች ኪሩቤል ፍጥረትን ይጠብቁ ዘንድ የሥላሴን መንበር ተሸክመው ይበራሉ በመቃርዮስ ትዕዛዝ ተፈጥረዋልና የመጀመሪያው መልአክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ባመለከታቸው ይሄዳሉ የገነት አስቄጥስ ሠራተኞች አራት ራስ ያለው አሞራ በባሕርይ አንድ ናቸውና ።

መወድስ ቅኔ

በዕለተ ዓርብ ቅድስት ዕለተ ፍስሐ በኪዳን እግር ይምጻእ ተክለ ሃይማኖት ሀገረትነ ፡

ተበርበረት ሲኦል ነዶተ ሥጋነ

እስመ ከመ ይኩንእም ሳሊሁ መቃርዮስ በኃይለ መስቀሉ ሰበከ ግዕዛነ ፡

ለተክለ ሃይማኖት እስመ ምጽ ዓቱ ስሑተነ ይሚጥ ወይምራህ ቅዱሳነ

ለዓለም

ይንግሥሂ እርእዮሁ ለዘፈጠ ረነ፡

ተክለ ሃይማኖት መሥተማህል ወሄር መምህርነ ፡

እምቅድመ ህሊና የእምር ተም ኔተ ልብነ ፡

እንበለ ንስእሎ በጸጋሁ ይሁብ ፍትወተነ ፡

ትርጓሜ

በዕለተ ዓርብ የደስታ ቀን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደሀገራችን መጣ በመጣም ጊዜ ሲኦል ችግራችን ተበረበረች ጠፋች መቃርዮስም እንደኤርሱ ይሆን ዘንድ በመስቀሉ ኃይል ነፃነትን አስተማረን ተክለ ሃይማኖት የመጣው በደለኞችን ወደጽድቅ ለመመለስ ጻድቃንን ለመምራት ነውና ፡

የፈጣሪያችን አርዓያ ይከተል ዘንድ ተክለ ሃያማኖት ቸር ይቅር ባይ መምህራችን ነው ከሁሉ አስ ቀድሞ የልቡናችን ያውቃልና ሳን ለምነው ፍላጎታችንን አውቆ ይሰጣናል ።

ከላይ እንደገለጽነው ለማስረጃ ያህል አቀረብን እንጂ የተነገሩትን ቅኔዎች ሁሉ በእትም ለማውጣት ቢፈለግ ራሱን የቻለ አንድ ታላቅ መጽሐፍ ለመሆን ይችል ነበር ።

ገዳመ አስቄጥስ በ፺ ዓመት ያሳየው ዕድገት እጅግ በጣም የሚያስደንቅ ሆኖ ተምልክተነዋል ፡ በይበልጥ ይህንን ገዳም ለቆረቆሩት ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ሀ ስበከት ሊቀ ጳጳስ ከፍ ያለ ደስታ ሊሰማቸው ይገባል ።

አንድነቱ የመምህራኑና የተማሮች ይዞታ የልማቱ እርምጃ ሁሉ ለሌሎች ገዳማትና አድባራት በትምህርት መልክ የሚጠቀስ ሆኖ አግኝተነዋል ገዳሙ በዚህ አንቅስቃሴው ብቻ ሳይወሰን ከዚህ በበለጠ ሠርቶ ለቤተ ክርስቲያናችን በዓርያነት ተጠቃሽ ሆኖ እንዲኖር የዘወትር ምኞታችን ነው ።

የዜናው አቅራቢ
ሊቀ ኅ ልሣን ወርቅ በዛብህ

# ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት

እግዚአብሔር ከዕለተ እሑድ ጀምሮ እስከ ዕለተ ዓርብ ድረስ ባሉት ፮ቀኖች በየወገን በየወገኑ የፈጠራቸው ስነ ፍጥረታት ፳፪ ሲሆኑ ከ፳፪ቱም መካከል መላእክት ናቸው ።

ቅዱሳን መላእክት ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን ለማገልገል የሰው ልጅ የጸለየውንም ጸሎት ለማሳረግና ለመንፈሳዊ ተልዕኮ የተፈጠሩ ቢሆኑም ሰውን እንዲረዱና የሰውን ችግር በተረዳኢነታቸው እንዲያስወግዱ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተሰጥቷቸዋል ።

ይኸንንም በማስመልከት መላእክት በተራዳኢነታቸው ምን ያህል ሥልጣን እንዳላቸው ሲገልጥ ቅዱስ ዳዊት (ይትአየን መልአከ እግዚአብሔር አውዶሙ ለእለ ይፈርህዎ ወያድኅኖሙ) እንዲህም ማለት "የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል መዝ·፴፫ ፡ ፴፬) ከዚህ የተነሣ ምእመናን ሁሉ እግዚአብሔርን በማመን በመላእክት አማላጅነትም በመማፀን ስማቸውን በመጥራት ስለ አምላክ ቅዱስ ሚካኤል ስለአምላክ ቅዱስ ገብርኤል እያሉ እየመጸወቱ በምድራዊ ዓለም ከመቅሠፍትና ከአደገኛ ሞት የሚድኑበት ሲሆን በበለጠ ደግሞ ተስፋ መንግሥተ ሰማያትን ያገኙበታል ስለዚህም ነው ቅዱስ ዳዊት የሚፈሩትን ያድናቸዋል ሲል የተናገረው ፡

የመላእክት ተራዳኢነት በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን በብዛት ተጠቅሶ ይገኛል ከብዙም በጥቂቱ ነቢዩ ዳንኤል የገለጸውን እንመልከት ፡

"የፋርስ መንግሥት አለቃ ሃያ አንድ ቀን ያህል ተቋቋመኝ እንሆም ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ቅዱስ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ ሲል ተራዳኢነቱን መስክሮ አናገኘዋለን ዳን·ም· ፲ ፲፪

የቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት በዚሁ አጭር ዓምድ ሊወሰንና ሊገለጽ ስለማይቻል ባጭሩ ለባሕራን ያደረገውን የድኅነትና የተራዳኢነት ታሪክ እንመለከታለን።

የቅዱስ ሚካኤልን ስም በማስታወስ በየወሩ በ፲፪ቀን የሚመጸውቱ ባልና ሚስት ነበሩ እነዚህ ሰዎች ጦቢት ለምጽዋት እጅህን ዘርጋ ከመመጽወትም ወደ ኋላ አትበል የሰው ምጽዋት ታድኅን እሞት" ምጽዋት ከሞት ታድናለችና ሲል እንደ ተናገረው እንግዶችን በመቀበል ድኾችን በመርዳት በጋለ መንፈስ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል በየወሩ ሲያከብሩ ወንዱ ከዚህ ዓለም በሞት የሚለይበት ጊዜ ሲደርስ ሚስቱን ጠርቶ እኔ ከዚህ ከኃላፊው ዓለም ወደ ማያልፈው ዓለም መሄዴ ነው ስለዚህ በሕይወት እስካለሽ ድረስ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል እንዳታስታጉዪ ዓቅምሽ በሚፈቅደው መጠን የቅዱስ ሚካኤልን በዓል እንድታከብሪ በማለት በአደራ መልክ ሚስቱን ተስናብቶ አረፈ።

ይህንን ቃል ነግሮ ተሰናበቷት ሲሄድ ግን ሚስቱ ፀንሳ ነበር ሚስቱም የባልዋን ቃል ሳታጥፍ በዓሉን እያከበረች አምላክዋን





www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔርን እየለመነችና በቅዱስ ሚካኤል አማላጅነት እየተማፀነች የፀነሰችውን ፅንስ ለመውለድ ምጥ ተያዘች በዚህ ጊዜ ከቅዱስ ሚካኤል በቀር ሌላ ዘመድ ስላልነበራት የቤትዋን ደጃፍ ዘግታ መስኮቶቹን ከፍታ በምጥ ተይዛ ሳለች የምሕረት አማላጅነት የተሰጠው ቅዱስ ሚካኤል በመስኮቱ ገብቶ አይዞሽ አትፍሪ አትደንግጭም ወንድ ልጅ ትገላገያለሽ እሱም በዚህ በጐረቤትሽ ያለውን ባለጸጋ ገንዘብና ንብረት ወራሽ ይሆናል ሲል አስደናቂ የሆነውን ነገር ነግሯት በዚያው በገባበት መስኮት ወጥቶ ሄደ ።

ቅዱስ ሚካኤል ለሴትየዋ ሲነግራት ባለጠጋው ከቤቱ ሆኖ ይሰማ ነበርና ይህ የምትወልጅው ልጅ የዚህ የጐረቤት ባለጸጋ ንብረት ወራሽ ይሆናል የሚለውን ድምፅ ሲሰማ ደነገጠ ፈራ ተንቀጠቀጠ ።

ባለጠጋው ምንም እንኳ በጐረቤትና ለብዙ ጊዜ ከሴትየዋ ጋር ቢኖርም አይወዳትም ነበር ይኸውም ሰድባው ወይም ኃይለ ቃል ተናግራው ሳይሆን በጎ ነገር በመሥራትዋ እየቀና ነበር ። ተንኰለኛ ሰው መቼም ሁልጊዜ ተንኰለኛ ነውና ሕፃኑ አድጎ የ፲ ዓመት ልጅ ሲሆን ይህንን ልጅሽን በጥሩ ሁኔታ እንዳሳድግልሽና እንዳስተምርልሽ ለእኔ ስጭኝ ላንችም ቢሆን በየወሩ የተወሰነ ደመወዝ እቆርጥልሻለሁ አላት ሴትየዋ ግን ስንኳንስ ራሱ ልጅሽን አሳድግልሻለሁ ሲላት ራስዋ እንኳ መለመን እንደሚገባት አውቃ የባለጸጋውን ተንኰል ሳትመለከት ልጅዋን አምጥታ ሰጠችው ።

ከዚህ በኋላ ባለ ጸጋው ልጁን በምን ዓይነት እንደሚያጠፋው ያወርድና ያወጣ ጀመር ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ግን ሳጥን ሠርቶ ከዚያው አሽጎ ወደ ባሕር ከመጣል ሌላ አማራጭ ስላልነበረው ። ጥሩ ሳጥን አሠርቶ ልጁን ከሳጥኑ ቆልፎ ወደ ባሕር ጣለው እግዚአብሔር ግን የሰውን ድኅነት እንጂ የሰውን ጥፋት ስለማይፈልግ የሚጠብቀው መልአክ ቅዱስ ሚካኤልን ስላዘዘለት ሳጥኑ እየተንሳፈፈ ወደ ሌላው ሀገር ሄዶ በባሕር ዳር ተንሳፎ ሳለ አንድ ሰው አየውና የነጋዴዎች ብር አገኘሁ ብሎ ሳጥኑን አውጥቶ ወደ ቤቱ ወሰደው ወድያውኑ ሰውየው ርቦት ነበር ወደ ዓሣ አጥማጆች ሄዶ ዓሣ ቢለምናቸው አንድ ዓሣ ሰጡትና ጠብሼ እበላለሁ ብሎ ሆዱን ቢቀደው ቁልፍ አገኘ ዓሣውን ከበላ በኋላ በዚያው ባገኘው ቁልፍ ሣጥኑን ቢሞክረው ተከፈተለት ቢያይ ፀሐይ የመሰለ ልጅ አገኘ ሰውየውም ልጅ ስላልነበረው ልጅ ይሆነኛል ብሎ ደስ ከመሰኘቱም ሌላ ከባሕር ስላገኘው ባሕራን የሚል ስም አወጣለት ።

ባሕራን በዚያው ሀገር ሲያገለግል ከኖረ በኋላ ያ በሣጥን አድርጎ ከባሕር የጣለው ባለ ጸጋ ለአንድ ጉዳይ መጥቶ ባሕራን ካለበት ቤት በእንግድነት አደረ ከዚህ በኋላ ባለቤቱ ባሕራንን እንዲህ አድርግ ባሕራን ይህንን አምጣ እያለ ሲጠራ ሰምቶ ባሕራን ማለት ምን ማለት ነው ብሎ ጠየቀና ባለቤቱም ይህ ጉዳይ ታሪክ ያለው ነው በዚህ ዓመተ ምሕረት በሣጥን ሁኖ ከባሕር የተገኘ ነው ሲለው ባለጸጋው ደነገጠ የተገኘበትንም ወርና ዓ·ም አጥብቆ ጠየቀው እሱም በትክክል ሲነግረው ለካ በሕይወት አለ አሁን እንዴት አድርጌ ልግደለው ይልና ባለጸጋው ያንን የባሕራንን አሳዳጊ ላንተም ለእሱም ብዙ ገንዘብ እሰጣችኋለሁና ይህ ልጅ ወደ አገሬ ሂዶ አንድ የረሳሁትን ዕቃ እንዲያመጣልኝ ብትፈቅድልኝ አለው ሰውየውም በተንኰል ስላልመሰለው እሺ ይሂድ ሲል ፈቀደለት ።

ባለፀጋውም እጅግ ደስ አለውና ደብዳቤ ጽፎ ይህ ልጅ ወዲያው እንደገባ ግደሉት የሚል ወረቀት አስይዞ ላከው ግን ቅዱስ ሚካኤል በመንገድ ቆይቶ ያንን ለሞት የተጻፈውን ደብዳቤ ለውጦ ይህ ልጅ እንደደረሰ ልጄን አጋብታችሁ ያለውን ሀብቴንና ንብረቴን እንድታወርሱት ወደሚል ተለወጠና ከቤት ደርሶ ደብዳቤው ሲነበብ በተጻፈው መሠረት የባለጠጋውን ልጅ አጋብተው ቤቱን አውርሰው ተድላ ደስታ ሲያደርጉ ባለጸጋውም አሁንስ ሙቶ ይሆናል እያለ በበቅሎው ላይ ተቀምጦ እየተሽከረከረ ሲመጣ የከበሮና የእምቢልታን ድምፅ ሰማና ይህ የምሰማው ጭኸት ምንድን ነው ብሎ በአካባቢው ያሉትን ሰዎች ቢጠይቅ ልጅህን ባሕራን ለተባለው ሰው አጋብተው ሀብትህንም ለሱ አውርሰው ስለ ዳሩት የዚያ ተድላ ደስታ ነው የምትሰማው ሲሉት ደንግጦ ከበቅሎው ተንኰታኩቶ ወድቆ ሞተ ይሞታል የተባለው ግን ዳነ ።

እንግዲህ ባሕራንን በረቂቅ ጥበቡ ያዳነ እግዚአብሔርን በማምለክ በተሰጠው የአማላጅነት ቃል ኪዳን ቅዱስ ሚካኤልን በመማፀን ቤተ ክርስቲያናችንን እናስፋፋ ሃይማኖታችንንም እናጽና

---

በሃይማኖት የፀና በመልአኩ አማላጅነትም የተማፀነ አያፍርምና።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ



# የጻድቁ የአቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ ታሪክ በአጭሩ

በገድላቸው በትሩፋታቸው የታወቁት የኢትዮጵያ ተወላጁ የሆኑት ጻድቁ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ በዋድላ ደላንታ አውራጃ በዳውንት ወረዳ ደብረ አሰጋጅ ከተባለው ቦታ ተወለዱ ።

አባታቸው ካህን መልአኩ እናታቸው ወለተ ማርያም ይባላሉ ጻድቁ በታኅሣሥ ፳ ቀን ተወልደው ፵ ቀን ሲሞላቸው ጥር ፲፯ ቀን ሲጠመቁ ስማቸው እስትንፋሰ ክርስቶስ ተብሎ ተሰይሚል ከአባታቸው ቤት በሥነ ሥርዓት አድገው ሰባት ዓመት ሲሞላቸው አባታቸው ኪራኮስ ወደ ተባሉት መምህር ወስደው አባቴ ሆይ ይህንን ልጄን ቤተ እግዚአብሔር አገልጋይ እንዲሆን በብፅዓትና በሥዕለት መልክ ስለሰጠሁት በሚገባ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት እንዲያስተምሩልኝ አደራ ብለው ሕፃኑን እስትንፋሰ ክርስቶስን አስረከቧቸው ።

መምህሩ ኪራኮስም ሕፃኑን ተረክበው የቤተ ክርብቲያንን ትምህርት አስጀምረው ንባብና ዳዊት ብሉያትንና ሐዲሳትን አስተምረው ሲፈጽሙ ለአባታቸው ለካህን መልአኩ አስረከቡአቸው አባታቸውም ወደ ጳጳሱ አቡነ ማርቆስ ወስደው ዲቁና እንዲቀበሉ በማድረግ ለተወለዱበት ለእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ሁነው እንዲያገለግሉ ሰጧቸው ጻድቁ እስትንፋሰ ክርስቶስም በተሌወለዱበት ደብር ብዙ ዘመን በዲቁና ማዕርግ ሲቀድሱ ከቆዩ በኋላ በፈቃደ እግዘአብሔር ከትውልድ ሀገራቸው መንነው ወደ ደሴተ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ሔዱ ከዚያም ከባሕሩ ዳር ሲደርሱ ጸሎት ካደረሱ በኋላ ያለ መርከብ ባሕሩን ተሻግረው ከደሴቱ ደርሰው በቤተ ክርስቲያኑ ሰግደው የተመስጦና የእንክር ጸሎትና ምስጋና ለፈጣሪያቸው አቅርበዋል በዚያ የሚኖሩ መነኮሳትም ያለመርከብ እንዴት ብለው ባሕሩን እንደተሻገሩ አድንቀው ሰላምታ አቀረቡላቸው ጻድቁ እስትንፋሰ ክርስቶስም መነኮሳቱን ወደ አበምኔቱ እንዲያቀርቡአቸው ጠይቀው አገናኙተዋቸዋል የሐይቅ ደሴት ገዳም አበምኔትም “መጻእከኑ ኀቤየ አወልድየ ከመትኩን መነኮሰ” ልጄ እስትንፋሰ ክርስቶስ ሆይ ወደ እኔ የመጣኸው መነኩሴ እንድትሆን ነው? አሏቸው ጻድቁ እስትንፋሰ ክርስቶስም አባቴ ሆይ አሳቤን አስቀድመው አውቀዋል በእርስዎ እጅ ልመነኩስ ነው የመጣሁት አሏቸው ።

የገዳሙም አበምኔት መጽሐፈ መነኮሳት እንደሚያዘው ፫ ዓመት በገዳሙ አበው መነኮሳትን እየረዱ ሥርዓተ ብህትውናን ሥርዓተ መነኮሳትን እየተከታተሉ እንዲቆዩ አዘዙአቸው

፫ ዓመት ሲሆናቸው መልካም ትሩፋታቸውና ምግባራቸው ተመርምሮና ተጠንቶ ወአልበሶ አልባሰ ምንኩስና ቅዱሳተ” ይላል ለቅድስና የምታበቃውን የምንኩስናን ማዕርግ ሰጥተው አመነኮሷቸው ፡

ቀጥለው ፪ኛ ሊቀ ዲያቆናት ሁነው በገዳሙ እንዲያገለግሉ መደቧቸው ከዚያም የገዳሙ መጋቢና ሊቀ ምርፋቅ እዲሆኑ በመልካም ተልእኮአቸው ብዙ ትሩፋት ሠርተው ከፍ ያለ ምስጋና አግኝተዋል በገዳሙ መነኮሳት ተመርጠው የቅስና የቁምስና የኩርልና ማዕረጋት ከጳጳሱ ከአቡነ ማርቆስ እንዲቀበሉ በማስታወሻ ተልዕከው ሶስቱንም ማዕርጋት ተቀብለዋል በነዚህም በተቀበሏቸው መንፈሳውያን ማዕርጋት በሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ሰባት ዓመት አገልግለዋል ጠቅላላም በሐይቅ ገዳም ፲፩ ዓመት ከአገለገሉ በኋላ “ወበጽሐ አድያመ ሺዋ ወመሐረ በህየ..” ይላል ከሐይቅ ገዳም ተነሥተው ወደ ሸዋ ምድር መጥተው የክርስቶስን ቸርነቱንና ሕግጋቱን የምትናገር ወንጌልን እየተዘዋወሩ አስተማሩ ። በመልካም አሰባበካቸውም የሸዋ ሕዝብ በደስታ ተቀብለው ትምህርታቸውን በሥራ ላይ አውለውታል ።

ከዚያም በዝቋላ ገዳም ፵ ቀን በጾምና በጸሎት በስግደት ሰንብተዋል በሱባዔው ፍጻሜም ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተገልጸው ካነጋገሯቸው በኋላ ተሠውረዋል ጻድቁ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስም በሸዋ ምድር አንድ ሺህ ሰባት መቶ ያልተጠመቁ ሰዎችን



www.ethiopianorthodox.org

አስተምረው በክረስቶስ ስም አሳምነው አጥምቀዋል ሰባት አብያተ ክርስቲያናትም አሳንፀዋል በዚህም በቅድስና ሥራቸው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ተገልጾ የእግዚአብሔር ባለሟል እስትንፋሰ ክርስቶስ ሆይ እግዚአብሔር አምላክህ ኢየሩሳሌም ሔደህ እኔ ሰውሁኝ በዚህ ዓለም ፴፫ ዓመት ከ፫ ወር የቅድስና ሥራ የሠራሁባቸውን ታሪካዊያንና ቅዱሳት መካናትን ተሳልሞና ስግዶ እንዲመጣ አዝገርዋለሁ ብሎሃል ብሎአቸው ተሠወረ ። ጻድቁ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስም ይህን የመሰለ መንፈሳዊ የምሥራች በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ቃል ሰምተው ደስ አላቸው ለእግዚአብሔርም ምስጋና አቀረቡ ።

በማግሥቱ ለመንገድ የሚሆናቸውን ሁሉ አዘጋጅተው ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞአቸውን ቀጥለዋል በመልአኩ መሪነት ኢየሩሳሌም ደርሰው ጌታችን የተወለደበትን ቤተልሔምን ያደገበትን ናዝሬትን የተጠመቀበትን ዮርዳኖስን ብርሃነ መለኮቱን የገለጸበትን ደብረ ታቦርን የጾመበትን ገዳመ ቆሮንቶስን የተሰቀለበትን ቀራንዮን የተቀበረበትን ጐልጐታን ጠቅላላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሁኖ ለሰው ልጅ ሲል የቅድስና ሥራ የሠራባቸውን ቅዱሳት መካናትን እየዞሩ በመሳለምና በመስገድ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅረበዋል ከዚያም ወደኢያሪኮ ሔደው ወደ አርማንያ ደሴት ለመሻገር ባለመርከቦችን እባካችሁ አሻግሩኝ ብለው ጠየቁአቸው እነሱም ገንዘብ ካልከፈልክ አናሻግርህም አሏቸው ።

ጻድቁ እስትንፋሰ ክርስቶስም ወደ እግዚአብሔር ጸልየው በጸሎታቸው ኃይል አጽፋቸውን በባሕሩ ላይ ዘርግተው ያለመርከብ ውሃ ሳይነካቸው ተሻግረው አርማንያ ገብተዋል በዚያም ከጻድቁ ከአቡነ ኤዎስጣቴዎስ መቃብር ላይ ጸልየው ወደ ግብፅ ሀገር ደርሰው በግብፅ ውስጥ የሚገኙትን ገዳመ አስቄጥስን የማርቆስን መቃብር እስክንድርያን የእንጦንስን መቃብር ተሳልመውና በዚያ የሕሊና ጸሎት አድርሰው ጠቅላላ በግብፅ በናግራን የሚገኙትን ቅዱሳት መካናትን ተሳልመው ወደአክሱም ተመልሰዋል በአክሱም ጽዮን ፴ ቀን በደብረ ሲና ሰባት ቀን በደብረ ቢዘን ሰባት ቀን ሱባዔ አድርገው ሰንብተዋል።

ከዚያም የተሰዓቱ ቅዱሳንን የጸሎት ቦታና የመቃብር ቦታቸውን ተሳልመዋል ።

ወደ ደብረ ዳሞ ገዳምም ሔደው ገድሉን ያለ ኃብል ወጥተው ብዙ ጊዜ ጸልየዋል ከዚያም ወደ ደብረ ዐባይና ወደ ዋልድባ ገዳም ሄደው ትሩፋት ሠርተዋል ከዚህ በኋላ ወደ ላስታ ሮሃ ሔደው በቅዱስ ይመርሃነ ክርስቶስና በቅዱስ ሐርቤ በቅዱስ ላሊበላ የመቃብር ቦታ ጸልየዋል ጻድቁ ቅዱስ ነአኩቶለአብ የተሠወረበትን ዋሻ ጐብኝተው የሕሊና ጸሎት አድርሰዋል ፣ ከዚያም በግሸን ዓንባ ላይ በሚገኘው ግማደ መስቀሉ ሰግደው የሕሊና ጸሎት አድረሰዋል በአማራ ሳይንት በገዳመ ገሸቅ በአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የመቃብር ቦታ በተድባበ ማርያም ሰግደው የሕሊና ጸሎታቸውን አድርሰዋል ።

ወደ ጐጃምና ወደ ቢገምድርም ተሻግረው ከጸጋ እስጢፋኖስና ከመሳሰሉት ደሴቶች ያለመርከብ እየተሻገሩ በመጐብኘት ጸልየዋል በዚያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾ አነጋግሯቸዋል ።

ከዚያም ተነሥተው ወደ ዞብል ሔደው ወንጌልን በማስተማር ብዙ ያልተጠመቁ ሰዎችን አስተምረው አሳምነው አጥምቀዋል ።

በዚያም ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሳንፀዋል ጠቅላላ በተዘዋወሩባቸው ታሪካዊ ቦታዎች ሁሉ ድውይ ፈውሰዋል ፣ ለምፅ አንፅተዋል ዕውር አብርተዋል መናፍስት ርኩሳንን አባረዋል ፤

"ወእምዝ ተፈነወ ገብርኤል መልአክ እምኀበ እግዚአብሔር ኀበ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ ወይቤሎ አፍቁረ እግዚአብሔር በጽሐ ጊዜ ዕረፍትከ ወሑር ኀበ ሙላደ ሀገርከ እንተ ይእቲ ጸውንት" ከዚህ በኋላ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ የእግዚአብሔር ወዳጅ እስትንፋሰ ክርስቶስ ሆይ ! የዕረፍትህ ዘመን ደርሷልና ተወልደህ ወደ አደግህባት ቦታ ወደ ጻውንት ተመለስ በዚያም አስጋጅ በሚባል ቦታ ተቀመጥ ብዙ መንፈሳውያን መነኮሳት ከየአውራጃው እየተሰበሰቡ ይመጡልሃልና እነርሱን እያስተማርክ የተለመደ ጸሎትህንና ስግደትህን እያደረግህ ኑር በእጅህም ብዙ ልዩ ልዩ ተአምር ይደረግልሃል የምትቀበርበትም ቦታ በዚሁ ደብረ አስጋጅ ነው በመቃብርህ አፈርም ድውይ ትፈውሳለህ አጋንንት ታባርራለህ ጠቅላላ ልዩ ልዩ ተአምር ትሠራለህ በመቃብርህም ላይ በ፳፬ቱ ካህናተ ሰማይ ስም ቤተ ክርስቲያን ይሠራበታል ብሎአቸው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ተሠወረ ።

ጻድቁ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤልን ቃል ሰምተው ምስጋና ለእግዚአብሔር በማቅረብ በግንባራቸው ተጐንብሰው በምድር ላይ ሰግደውና ጻድቁ እስትንፋሰ ክርስቶስ ከዞብል ተነሥተው ተወልደው ወደአደጉባት ወደ ጻውንት ተመልሰው ሄደው የእግዚአብሔር አብን ቤተ ክርስቲያን እያጠኑ በጾም በጸሎት በስግደት ተወስነው ደብረ አስጋጅ በሚባል ልዩ ቦታ በዓታቸውን አድርገው ተቀምጠው ሳለ መልአኩ እንደነገራቸው ከየአውራጃው ብዙ መንፈሳውያን መነኮሳት እየመጡ ከአቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ ዘንድ ይማሩ ጀመር ፤

ምግባቸውንም የሚመገቡትወ ያወርድ እምሰማይ ኀበስተ ዩና ኤል መልአክ ይላል መልአኩ ቅዱስ ዩናኤል ከሰማይ ኅብስት እየመላለሳላቸው ያን ይመገቡ ነበር እንጅ በሰው እጅ የተሠራ አይመገቡም ነበር ይላል ገድላቸው ።

ከገዳመ ግሸትና ከገዳመ ዐበለጐል አቡነ አካለ ክርስቶስ አባ ቴዎጐስ ከደብረ ዳሬት ከገዳመ ማጋ ወለቴ አባ ሥነ ድንግል አባ ልብሰ ክርስቶስ የሚባሉ የበቁ ቅዱሳን መነኮሳት እየመጡ ከጻድቁ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ ጋር ይቀመጡ ጀመር ።

ወተሰምዓ ዜናሁ ለአቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ ውስተ ኩሉ በሐውርት ይላል የጻድቁ የእስትንፋሰ ክርስቶስ የቅድስና ሥራቸው በየአውራጃው ሁሉ ተሰማ በዚህም ምክንያት ከየአውራጃው ሁሉ እየመጡ ከጻድቁ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ የሚማሩትና የሚባረኩት ከመብዛታቸው የተነሣ ተማሮቻቸው ሁሉ እስከ አሥር ሺህ ደርሰው እንደነበር መጽሐፈ ገድላቸው ይናገራል ።

በዚህም ዝናቸው ንጉሡ ዓጼ ፋሲል ልጃቸውን ዮሐንስን አመጥተው ቡራኬ በማስቀበል አባቴ ሆይ ይህ ልጅ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ረጋ ያለ ጭምት ስለሆነ የበለጠ መንፈሳዊ እንዲሆን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትንና መልካም ምግባርን ያስተምሩልኝ ብለው ከእርሳቸው ቀጥለው የሚነግሡትን ዮሐንስ ጻድቁን ሰጥተዋቸዋል ።

ጻድቁ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስም የንጉሡን የዓጼ ፋሲልን ልጅ ጻድቁ ዮሐንስን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትንና ምግባር ትሩፋትን አስተምረው ለንጉሡ አጼ ፋሲል አስረክበዋቸዋል ፤

ንጉሡም በሕይወታቸው ሳሉ ከእኔ ቀጥሎ የሚነግሠው ይህ ልጄ ዮሐንስ ነው ብለው በተናገሩት መሠረት ከአባታቸው ከዓጼ ፋሲል ቀጥለው ዮሐንስ ቀዳማይ የመጀመሪያው ተብለው ነግሠዋል በዘመነ መንግሥታቸውም ሲኖሩ እንደ ቅዱሳን ሁነው የምናኔ ሥራ ሲሠሩ እንደኖሩ የራሳቸው ቀዳማዊ ዮሐንስ ዜና መዋዕል ያስረዳል ።

በገድለ እስትንፋሰ ክረስቶስ ተጽፎ እንዳገኘነው ዓፄ ዮሐንስ የአቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ የጸሎት ቦታ አካባቢና በሙሉ ጻውንት ጻሩ እሳት መሐሉ ገነት ይሁንልዎ ብለው ሰጥተዋቸዋል ጠቅላላም የኢትዮጵያ ምእመናን በሙሉ የጻድቁ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ የጸሎት ቦታ ብለው በተቀመጡበት ቦታ እየሔዱ እንዲሰግዱ በተጨማሪም መወሰናቸው ገድለ እስትንፋሰ ክርስቶስ ይናገራል ።

በዚህም ምክንያት የአቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ የመቃብር ቦታ ደብረ አሰጋጅ ተብሎ ተሰየመ ፤

ጻድቁ እስትንፋሰ ክርስቶስም የርሳቸው ረዳት እንዲሆኑ አባ አካለ ክርስቶስን ሊቀ ጉባኤ አድርገው የትምህርቱ ጉባዔ ሳይቋረጥ እስከ ሕይወት ፍጻሜአቸው ድረስ ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍርተው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን አስረክበዋል ። የአንድነት የንፋሮ ገዳም አቋቁመው መሥርተዋል ።

ከዚህ በኋላ ወዜነዎ መልአከ እግዚአብሔር ለአቡነ እስትፋሰ ክርስቶስ ጊዜ ፍልሰቱ እምዛቲ ዓለም ለዕለት ወለሰዓት ለወርኅ ወለዓመት ይላል ጻድቁ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ ከዚህ ዓለም የሚለዩበት ሲቃረብ የሚያርፉበትን ሰዓቱንና ዕለቱን ወርኁንና ዓመቱን ለይቶ ነገራቸው ጻድቁም ይህን ቃል ከመልአኩ እንደሰሙ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸውን ሰብስበው በነፍስ በሥጋቸው የሚጠቀሙበትን በማስረዳት ከመከሩአቸው በኋላ ፤

ሚያዝያ ሁለት ቀን ታመሙ ጻድቁም ጊዜ ዕረፍታቸው እንደደረሰ አውቀው ወደ ፈጣሪያቸው ክርስቶስ እንዲህ ብለው ጸለዩ ጌታዩ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ስሜን የጠራ ዝክሬን የዘከረ በአንተ አምኖ በስሜ የተማፀነ ሁሉ ለእኔ አሥራት እንዲሆነኝ ትስጠኝ ዘንድ እለምንሃለሁ ብለው ጸለዩ ጌታም ለጻድቁ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ ተገልጸ ወዳጄ እስትንፋሰ ክርስቶስ ሆይ !ስምህን





www.ethiopianorthodox.org

የጠራ ዝክርህን የዘከረ በእኔ አምኖ በስምህ የተማፀነ እስከ ፲፯ ትውልድ ድረስ አሥራተ ምህረት ሰጥቸሃለሁ ይህች የመቃብር ቦታህ እስከ ዳግም ምጽአቴ ድረስ የተባረከችና የተቀደሰች ትሁን ልህ ብሎአቸው ሲፈጽም ባርኳቸው ተሠወረ ፡

ከዚህ በኋላ ሚያዝያ ፱ ቀን በዕለተ ዓርብ በአድያም ሰገድ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት በ፹፱ ዕድሜአቸው አርፈው በዚሁ ብዙ ትሩፋት በሠሩበት በደብረ አሰጋጅ በክብር ተቀብረዋል ። ነፍሳቸውንም መላእክት ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር እያሉ ወደ ሰማይ ሲያሳርጓት የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው ለማየት ችለዋል ።

ከዚህ በኋላ አንድ አባ አትናቴዎስ የተባሉ የበቁ ቅዱስ መነኩሴ ታቦተ ክህናተ ሰማይን ይዘው ከግሸን አንባ እግዚአብሔር አብ ተነሥተው መጥተው ጻድቁ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ ከተቀበሩበት ላይ ይህን ታቦት አስቀምጣችሁ ጸልዩበት ብለው ያመጡትን ታቦት ለመነኮሳቱ አስረክበው ከፊታቸው ተሠውረዋል ። ገዳላቸውንም አባ አካለ ክርስቶስ የተባሉት ቅዱስ መነኩሴ ጽፈውላቸዋል ።

መነኮሳቱም እግዚአብሔርን አመስግነው ከዚያም አያይዘው በጻድቁ እስትንፋሰ ክርስቶስ መቃብር ላይ ታላቅ ቤተ መቅደስ ሠርተው ታቦተ ክህናተ ሰማይን አስገብተው ቅዳሴ ቤቱን ሚያዝያ ፱ ቀን አከበሩ መነኮሳቱም በተን በቀን ጸሎተ ዕጣን እየጸለዩ ፳፱ መነኮሳት እየሆኑ ያጥኑ ጀመር ከዚህ ሌላ የመዓልትና የሌሊትም ሰዓታት ዘወትር እንዲቆምብት ወሰኑ በዚህ ሁኔታ በገዳሙ እስከ ዓጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ድረስ አበው መነኮሳት ሳይለዩ ብዙ ትሩፋት ሲሠሩበት ኑረዋል ከዚያም ወዲህ ቢሆን እንደጥንቱ ብዙ መናንያን መነኮሳትም ባይገኙበትም በመጠኑ መናንያን ባሕታውያን ይገኙበታል ዛሬ በዚህ ታላቅ ጻድቅ በዓለ ዕረፍት ሚያዝያ ዘጠኝ ቀን በየዓመቱ የሚገኘው ተሳላሚ ምእመን እጅግ ብዙ ነው ከመቃብራቸውም አፈር እየተቀባ የሚፈወሰውም ሕዝብ ስፍር ቁጥር የለውም የመቃብራቸው አፈር ለቁስልና ለአንበጣ ለበረዶ የታወቀ መድኃኒት ስለሆነ የመቃብራቸውን አፈር የሚወስደው ምእመን እጅግ ብዙ ነው ።

ለጸሎት ከቆሙባቸው ከአራት ቦታ ላይ የፈለቀው ጸበል አምሳለ የርዳኖስ ነው እየተባለ ሰው ሲጠመቅ የታመመ ሁሉ ይድንበታል ይህ ታሪካዊ ቦታ የሚገኘው ደላንታ ውስጥ ስለሆነ ከደላንታ እስከ እስትንፋሰ ክርስቶስ ገዳም ድረስ በበጋ መኪና ይገባበታል ፡

ቦታው ወይና ደጋ ሆኖ ከጥግ ቦታ ላይ የሚገኝ ሲሆን የጨቅ ፀሐይ በቶሎ የሚጠባበት ለጤና ተስማሚ ቦታ ነው የዚህ ሀገር ሕዝብ ሥራ ወዳጅ ገበሬ ስለሆነ አህል ችግር ብዙ ጊዜ አያውቅም በዚህ ምክንያት የዜማና የቅኔ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ሲሉ በዚያ እያስተማሩ ይኖሩበታል ብዙ ደቀ መዛሙርትንም አስተምረው ያወጥኑበታል ፡

እንግዲህ የዚህን ታላቅ ጻድቅ የቅድስና ሥራ ገልጸንላችኋልና ወደዚያው ቦታ እየሄዳችሁ በረ

# ዜና ዮሐ እ....

(ከገጽ ፯ የዞረ)

በዚህ ዓይነት ከተማረና ካወቀ በኋላ በዚህ ዓለም ላይ የሚኖሩ የሰው ልጆች ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን ያለአግባብ አስፈላጊ ባልሆነ ቦታ እንዳያውሉና እንዳያባክኑ ያስተምራቸውና ይመክራቸው ነበር ። በዚህ ሁሉ ቀን ከሴሊት ድሆችን ያገለግል ነበር ።

ከዚያም በሌላ አካባቢ ለጥቂት ዓመታት ያህል በመዘዋወር የተለያዩ ነገሮችን በማጤን ከቆየ በኋላ ለሁለት ዓመት በዋሻ ውስጥ ዘግቶ በመጸለይ ወደ ፊት ስለሚፈጽመው አገልግሎት መመሪያ ከፈጣሪው ተቀብሏል ።

እንዲሁም ይህንን የጸሎት ፕሮግራሙን ከጨረሰና ከፈጣሪው መመሪያውን ከተቀበለ በኋላ ወደ ተወለደበት ቦታ ተመልሶ አገልግሎቱን በመጀመር ማስተማሩን ተያያዘ ። ዮሐንስ አፈወርቅ የዲቁናን መዓርግ በተቀበለ በአሥር ዓመቱ የተለያዩ ድርሰቶችን ጽፏል ። ከዚህም ውስጥ ስለመነኮሳት ስለ ሥልጣነ ክህነትና ስለመንፈሳዊ አገልግሎት ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ሕግጋት በማስመልከት በሚገባ በመዘርዘር ገልጿታል ።

ከዚህም ሌላ የቅስና መዓርግን ከተቀበለ በኋላ ከመጀመሪያ ይዞታው አስበልጦ ስለአስተማረ በትምህርቱና በእውነተኛ አቋሙ እጅግ በጣም የተወደደና ዝነኛ

(ወደ ገጽ ፳ ይዞራል)

ከት ተቀበሉ ለሁላችንም እግዚአብሔር አምላካችን ከጻድቁ ረድኤት በረከት ያሳትፈን ።

የታሪኩ አቅራቢ አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ ዘገነተ ማርያም



# ቅድስት አፎምያ

*የፈትር እግዚአብሔር ጽድቀ ወምጽዋተ መዝ ፴፪.፭*
*እግዚአብሔር እውነት ነገርንና ምጽዋትን ይወዳል ።*

ይህን ቃል የተናገረው ነቢዩ ዳዊት ነው ። ነቢዩ ዳዊት ይህን ቃል ለመናገር የበቃው እግዚአብሔር አምላኩን በፍጹም ልብ በፍጹም ነፍስ ይወደው ስለነበረ ድንቅ ሥራውንም ይከታተል ስለነበረ ነው ። በዚህ ቅዱስ ቃሉ ፡ ነቢዩን የተከተሉ ብዙ ሰዎች ክብረ ሥጋንና ክብረ ነፍስን እንዳገኙበት ይነገራል ። ክብረ ነፍስን ካገኙት ሰዎችም አንዷ ቅድስት አፎምያ ናት እርሷም በሕግ ተወስና መንፈሳዊ አላማውን በማጠናከር እጇ ከምጽዋት እንደበቷ ከጸሎት ፡ ሳያቋርጥ እንዲሁም እንግዶችን በመቀበል ፡ የቅዱሳንን እግሮችን በማጠብ ፡ የተቸገሩትን በመርዳት ፡ በአጠቃላይ በጐ ምግባሯ የተመሰከረላት ፡ መልካም ዝናንም ያተረፈች ቅድስት ሴት ነበረች ።

ይችውም ቅድስት ሴት በዚህ ዓለም ከአንድ ደግ ሰው ጋር ትዳር መሥርታ ቤት ሠርታ ጐመን ዘርታ ፡ መኖር ስትጀምር ባልና ሚስት ከአንድ ባሕር ይቀዳሉ እንደተባለው የሁለቱ ባልና ሚስት አላማ ከዚህ ዓለም ተግባር የራቀ ፡ በመንፈሳዊ አእምሮ የተራቀቀ ሆነ ከዚህ የተነሣ ፡ ቅድስት አፎምያ ገርና ትን የሆነውን የባሏን ትእዛዝ ታከብር ፈቃዱንም ትፈጽም ፡ ምክሩን ትሰማ ነበር ። በአንጻሩ ይህ ደግ ሰው ባለቤቱም የሚስቱን ምክር ባለማቃለል ይቀበል ነበር ስለዚህ የሁለቱም መንፈሳዊ ጉዞ መናናቅና መለያየት ሳይኖርበት አንድ ዓይነት በመሆኑ ለበጎ ምግባራቸው አመች ሆነላቸው ።

ስለዚህ ገንዘብህን በከንቱ አትበትን የሰውነትህንም ፈቃድ ብቻ አትከተል ሲራክ ፳፥፪ ያለውን ትምህርታዊ መግለጫ በዓይነ ሕሊና አንብበው በተግባር በመተርጐም ከልዑል እግዚአብሔር በጸጋ የተሰጣቸውን ገንዘብ ወርቅና ብራቸውን በማይጠቅም ነገር ሳያውሉ ማለትም ለጣዖት ፡ ለቃልቻ ፡ ሳይገብሩ ፡ በልዩ ልዩ ዓለማውያን ጌጣጌጦች ሳያከስሩ ይልቁንም ነቢዩ ዳዊት ፡ በተናገረው ለችግረኞችም ሰጠ ጽድቁም ለዘላለም ይኖራል መዝ ፻፲፩.፱ ያለውን ትምህርታዊ ቃል በመገንዘብ ባንዲት ምክር ተስማምተው ያለ ንብረታቸውን ወርቃቸውንና ብራቸው ለችግረኞችና ለጦም አዳሪዎች መመጽወት ጀመሩ ።

ሲመጸውቱም ፡ የቅዱስ ሚካኤልን ፡ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በዓል ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ የተወለደበትን የመታሰቢያ በዓል በየወሩ ለመሥዋዕት የሚሆነውን መገበሪያ ዕጣን መብራት ዘቢብ በማቅረብ እንዲሁም ለችግረኞች ጸበል ጸዲቅ አዘጋጅተው በመመገብ ነበር ።

ቅድስት አፎምያና ባለቤቷ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው ቆሮ ፯.፯ በተባለው ቃል ይህን በመሰለ የተቀደሰ በጐ ምግባር ተወስነው ሲኖሩ የሰው ልጅ በበጎ ምግባሩ በሌላ ዓለም እንጅ በዚህ ዓለም ሞትን ሳያይ ፡ ሕያው ሆኖ መኖር ፡ ስለማይችል መዝ ፹፰. ፵፰ የቅድስት አፎምያ ባለቤት ታመመና ከሕማሙ ጽናት የተነሣ የሞቱ ቀን እንደተቃረበ ተገንዝቦ ነፍሱ ከሥጋው ከመለየቷ በፊት ባለቤቱን ጠርቶ የቀድሞውን ሥራቸውን ፡ እስከ ዕለተ ሞቷ ድረስ ፡ እንዳታቋርጥ በማጽናት አበረታት አጽናናትም ቅድስት አፎምያም የባሏን ቃል አከበረች በጎ ሥራዋንም ከቀድሞው ይልቅ አብልጣ ሠራች እንዲሁም በጾምና በጸሎት በምጽዋትና በስግደት ፡ የሥጋዋን ኃይል በማድከም አካሄዷን ሁሉ ከምትወደው ልዑል እግዚአብሔር ጋር በማጣመር ከፍጹማን ደረጃ ደረሰች ።

የቅድስት አፎምያ በጎ ምግባር ከዕለት ወደ ዕለት ፡ እያደገ ስለ ሄደ፡ ጸላዔ ሠናያት ሰይጣን በቅንዓት መንፈስ ተበርዞ በአፎምያ ቀና መንገድ ላይ የማሰናከያ ድንጋይ ለማኖር ብዙ ጥረት አደረገ ጥረቱም የሚሳካበትን መንገድ ሲፈልግ አንድ ነገር ትዝ አለው እሱም በፊት ለፊት ሳይሆን በምሳሌ መቅረብ ነበር ። አንድ ቀንም፡ መበለት መነኩሴት (መስሎ ወገቡን አጉብጦ ፡ መቋሚያ ጨብጦ ተከናንቦ ድምጹን ሰልቦ ቀርቦ አፎምያ እንደምት አለሽ አላት እሷም ባደረባት መንፈስ ጥበብ ተመራምራ ማን እንደ ሆነ ስለደረሰበችበት በንቀት ቃል ምን ነበር አለችው እኔ ላንቺ ሳስብ ልሽ ብዙ ጊዜ ነው ይኸ የምትከተይው ሥራ ሥራፈት አስኝቶሻልና ይህን የሥራ ፈቶች ሥራ ወዲያ ወርውረሽ ጥለሽ ይልቁን የሚጠቅምሽን ባል አግብተሽ ኑሮ መሥርተሽ ብትኖሪ ፡ የተሻለ ይመስለኛል አላት ቅድስት አፎምያም ሥነ ሥርዓት በተመላው አነጋ



www.ethiopianorthodox.org

ገር፡ ሲመለከቱዎት መንኩሴት ይመስላሉ በንግግርዎት ደግሞ የወናብዳሉ ይኸን ዓይነት የሰይጣን ምክር ይዘው ከፊቴ ዘውር ይበሉ በማለት የኃፍረት ማቅ አከናንባ መለሰችው ሰይጣንም ወጥመዱ ስላልተሳበለት ፡ በመናደድ እናትሽ ሔዋንም ከእኔ ማምለጥ አልቻለችም እንኳን አንች በማለት ለጊዜው ዘውር አለ ።

ቅድስት አፎምያም ሰይጣን ትግሉን መቀጠሉ እንደማይቀር ተገንዝባ ፡ በበጎ ሥራዋ ላይ በጎ ሥራ በመጨመር የተለመደ መንፈሳዊ ጉዞዋና ቀጠለች ። በሥራዋ ሁሉ እንደ ፀሐይ አበራች ። በጾጋ ላይ ጾጋ ተጨመረላት ስለዚህ ጠላት ሰይጣን ፡ ተናድዶ የሚአደርገውንም አጣ ሌላ መንገድ ቀየሰ ሲያወጣ ሲያወርድም ጠንካራ ጠላት የሚሸነፈው በወዳጅ መሆኑን ተገነዘበ በዚህ ረገድ ወዳጇን አማላጇን ቅ ሚካኤልን መስሎ ሥራዊተ ሚካኤልን የመሰሉ ሥራዊት አስከትሎ ቅድስት አፎምያ ፡ ከጸሎት ቤቷ ገብታ ስትጸልይ ከተፍ ብሎ አፎምያ እንዴት አለሽ እኔ ወዳጅሽ የመላእክት አለቃ ቅ ሚካኤል ነኝ ምን እንቺ የወዳጅ ምክር አትቀበይ ለምን ይኸን ብቻ መኖር ትተሽ ፡ ወደ ዓለም ፡ ተመልሰሽ ገንዘብሽ ሳይ ልቅ ባል አግብተሽ ቤት ሥርተሽ የምትወዷውን እንግዳ እየተቀበልሽ እንደአባቶችሽ እንደነ አብርሃም እንደነይስሐቅ እንደነያዕቆብ እንደነዳዊት አትኖሪም አላትቅድስት አፎምያም አሁንም የሰይጣኑን ተንኮል ስለተገነዘበች ከተቀመጠችበት መነኑ ጸሎት አፈና ብላ ተነሥታ ፡ እረ ለመሆኑ አንተ ማነህ ቅ ሚካኤል ነኝ ብልሃል ቅ ሚካኤል ከሆንክ ፡ ከአንተ የመስቀል ምልክት ወዴት አለ የአንድ ንጉሥ ወታደር የንጉሡን ምልክት ሳይዝ ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር አይችልም ብላ እንደ ጠበቀበት ባለቤቷ አስሎ የሰጠኝ የቅ ሚካኤል ሥዕል በቤቱ ውስጥ ስላለ አምጥቼ ላሳይህ ብላ መንገድ ስትጀምር ተንኮለኛው ሰይጣን እንደነቃችበት አውቆ መልኩን ለውጦ በስውነቷ ላይ አደጋ ለማድረስ ሲሞክር ቅድስት አፎምያ ፡ ወደ ወዳጁ ቅ ሚካኤል ሆሆ ብላ አማጸነች ። ቅ ሚካኤልም ጭሆቷን ለመናዋን ሰምቶ ፈጥኖ ደረሰላት ከሰይጣንም እጅ አዳናት ። ከዚህ በኋላ ሌባ ተያዥ ዱላ አይጠየቅም እንደተባለው የመላእክት አለቃ ቅ ሚካኤል ስምህ በተጠራበት ቤተ ክርስቲያ ንህ በታነጸበት በስምህ የተማጸኑ ክርስቲያኖች ባሉበት ሁሉ አልደርስም እስቴ ልድረስ በእግሬ እሳት ረግጦ በብረት መስቀል ቀጥቅጦ አሳደደው ።

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ሚካኤል ቅ አፎምያን በዚህች ዕለት ከዚህ ዓለም ትለያለሽና እግዚአብሔር በጎ ምግባርሽን ተቀብሎ ምጽዋትሽን ጸሎትሽን ሰምቶ ዓይን ያላየውን ጆሮ ያልሰማውን በሰው ልብ ያልታሰበውን መንግሥተ ሰማያት አዘጋጅቶልሻልና ተዘጋጅ ብሏት ወደ ሰማይ አረገ ቅ አፎምያም በጊዜው የነበረውን ኤጲስ ቆጶስ ከካህናትና ከዲያቆናት ጋር አስጠርታ ከገንዘቧ በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ሲሶ ለነዳያን ሲሶ ለካህናት ሲሶ ለቤተ ክርስቲያን መጽውታ ከመጸወተች በኋላ የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል በፊቷ አድርጋ ጸሎት አድርሳበት ሥዕሉን ከደረቷ ላይ እንዳ ስቀመጠች ከዚህ ዓለም ፃማና ድካም ሰኔ ፲፪ ቀን አረፈች ።

እንባብያን ከዚህ በላይ ያለውን ቅድስት አፎምያንና ባለቤቷን ስለበጎ ሥራቸው የመላእክት አለቃ ቅ/ሚካኤል እንዴት እንደ ተራዳቸው አንብበናል እንግዲህ አንባቢው ያስተውል ማቴ ፳፬. ፶፩ በተባለው መሠረት ማንበብ ለማስተዋል ነው ማስተዋል ደግሞ ጥቅምንና ጉዳትን አጣርቶ ለማወቅ ነው ይህን ካወቅን ልዑል እግዚአብሔር ከሁሉ ይልቅ ነቢዩ ዳዊት እንደተናገረው እውነት ነገርንና ምጽዋትን ለሚ ወዱና ለሚመጸውቱ በመላእክት አማካይነት ምን ያህል እንደሚ ረዳ ተገንዝበን እኛም ለዚህ ለተ ቀደሰ በጎ ምግባር በፍጹም ልብና በቅን መንፈስ መሰለፍ ይኖርብ ናል ለዚህም ልዑል እግዚአብ ሔር ይርዳን አሜን ።

መልአከ ኃይል ናሁ ሠናይ
ወርቅነህ



## ዜና ሊቃውንት

# መልአከ ጽዮን ጥሩነህ በጎሰው ፵፰ ዓመት ያስተማሩ ፶፪ ዓመት በትዳር የኖሩ :

መልአከ ጽዮን ጥሩነህ በጐሰው በጐንደር ክፍለ ሀገር ፡ በጋይንት አውራጃ በስማዳ ወረዳ ዝርጋ ሙጇ በተለይ ደብረ ጽዮን ማኝ መሬ ማርያም በተባለችው ደብር ከአባታቸው ከአቶ በጐሰው ካሳዬ እና ከእናታቸው ከወ ሮ በኋላ እማ ሆይ ቦጋለች ደሻል ግንቦት ፲ ቀን ፲፰፻፸፩ ዓ.ም ተወለዱ ።

እድሜያቸው ለትምህርት እን ደደረሰ ከፊደል እስከ ውዳሴ ማር ያም እና ዳዊት እጅግ ታዋቂና ስመ ጥር ከነበሩት የደብሩ የዝ ማሬ መዋሥዕት መምህር ወልደ ትንግኤ ይልማ ንሕብ አዝላ ማር ያም ከተማሩ በኋላ በመቀጠል ጾዋትወ ዜማ ማለትም ጾመ ድጓ ፡ ከእርሳቸው አጠናቀው ተምረው እንደጨረሱ ስማዳ ከመምህር በትሩ ቅኔ ተምረው ለራሳቸው ያህል አወቁ ።

እንዲሁም ገና በ፲፪ ዓመት ዕድ ሜያቸው ወደ አዲስ አበባ ከታላቅ ወንድማቸው ከአቶ ዳኛው በጐ ሰው ጋር መጥተው ዲቁና ተቀ በሉ ።

የትምህርት ፍላጐታቸው እየ ጨመረ በመሄዱ እዚያው ስማዳ ወረዳ ውስጥ ጋላ ጐዳና ኪዳነ ምህረት መምህር ካሣ ይሻል ከተባሉት ቅዳሴ ተምረው በመም ህርነት ተመርቀዋል ። ከዚያ በኋላ ወደትውልድ ቀበሌያቸው ተመል ሰው ግንቦት ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፯ ዓ.ም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የክህነት ሥርዓት ጋብቻ መሠረት ወ ሮ አስረስ ወር ቅነህ (አሁን እማሆይ) ከተባሉት ጋር ሥርዓተ ጋብቻ ፈጸሙ ።

በ፲፱፻፴፩ ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው ማዕረገ ቅስና ተቀ ብሉ ። መልአከ ጽዮን ጥሩነህ በጐሰው ከትምህርት ቤት እንደተ መለሱ "ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ" ባለው አምላካዊ መመ ሪያ መሠረት ወንበር ዘርግተው ከፊደል እስከዜማ በተለይ ሥር



መልአከ ጽዮን ጥሩነህ እሼህ ነበሩ

ዓተ ቅዳሴ በማስተማር ቆላማ ሆነው በአገልጋይ ካህናት እጦት ለተቸገሩት አብያተ ክርስቲያናት የነበረውን ችግር በማስወገድ በቲ አገልጋይ ካህናትን አበርክተ ዋል።

በመሠረታዊ የዲቁና ቅስናና መረጌትነት ያስተማሯቸው ከ፳፻ በላይ እንደሚሆኑ እኔ የዚህ ታሪክ አቅራቢም በመማር ላይ ስለነበ ርኩ የዓይን ምስክር ነኝ ፡

መልአከ ጽዮን ጥሩነህ ወንበር ዘርግተው በሚያስተምሩበት ወቅ ትም የራሳቸውን ትምህርት መከ ታተል ችል አላሉም ። በዚህም መሠረት በቀድሞው ጊዜ በነበ ረው አከፋፈል ለአስተማሪናታ ቸው እና ለመረጌትነት በዓመት የሚያገኙትን እህልና ጥሬ ገንዘብ ለየመምህራኑ በመፍቀድ እርሳ ቸው በነፃ እያገለገሉ መምህራኑ ወደ እርሳቸው ቦታ እየሄዱ ወን በር ዘርግተው እንዲያስተምሩ በማድረግ ቀረ ትምህርታቸውን ይከታተሉ ነበር ። በደመወዛቸው እየቀጠሩ እንዲያስተምሩዋቸው ካደረጉዋቸው መምህራን መካ ከል ፡

፩ኛ መምህር ገብረ ሥላሴ የድጓ የአቋቋምና የመጻሕፍት ትርጓሜ ሊቅ ፡

፪ኛ ዝማሬ ማዋሥዕት እና አቋ ቋም በማጠናከር ከመምህር አወቀ እና ከመምህር ዘውዴ ፡

፫ኛ ከመምህር ሠይፉ ቅኔ ከነአ ገባቡ በማጠናከር እና ሌሎ ችም ስማቸው የተዘነጋኝ መምህ ራን እንዳችው ለተው ሲሄዱ ሌላ ውን በመተካት ደመወዛቸውን እየከፈሉ እርሳቸው ግን በነፃ በማ ስተማርና ቤተ ክርስቲያኑዋን በቅ ንነት በማገልገል ለ፵፰ ዓመት ቆይተዋል ።

መልአከ ጽዮን በሚኖሩባቸው



www.ethiopianorthodox.org

አካባቢዎች የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት መሪጌታ የሌላቸው በመሆናቸው በየዓመት በዓሉ እየ ተዘዋወሩ በመሪጌትነት በማገል ገል ተወዳጅነትን ያተረፉ ነበሩ ።

በዚሁ ቅን አገልግሎታቸው ከ፲፱፻፵፪ ዓ.ም ጀምሮ የታች ሙጃ ም/ሊ.ቀ ካህናት ሹም ሆነው በማገ ልገል ላይ እንዳሉ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል የጐንደር ሀገረ ስብከት ሊ.ቀ ጳጳስ የነበሩት ግሸን ማርያም ድረስ ጠርተዋቸው የጀመሩትን አገልግሎትና ማስተማር እንዲገ ፉበት አበረታተው ሽልማት ሰጥ ተዋቸዋል ።

በ፲፱፻፵፰ ዓ.ም በብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊ.ቀ ጳጳስ ከነበሩት የስማዳ ወረዳ ቤተ ክህነት ሹም ሆነው ተሹ መው እስከ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም አገልግ ለው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጡረታ ቢገለሉም የማስተማር ተግባራቸ ውን ሳያቋርጡ እስከ ፲፱፻፸፮ ዓ.ም ድረስ በድምሩ ፵፰ ዓመት አስተ ምረዋል ።

በጡረታ ተገልለው በማስተ ማር ላይ እንዳሉ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያ ርክ ርዕሰ ሊ.ቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮ ጵያ ፈቃድ የተወለዱባት ገጃመሬ ማርያም "ደብረ ጽዮን" ተብላስ ትደበር እርሳቸው የመጀሪያው መልአከ ጽዮን ሆነው ተሾመው

እስከ ዕለተ ሞታቸው አገልግለ ዋል ። መልአከ ጽዮን ጥሩነህ በጐሰው በሕዝቡ ዘንድ እጅግ ተወዳጅና ጾም ጸሎት አፍቃሪ እግዚአብሔርን ፈሪ በስብከት ትምህርትም የበሰሉና በየበዓላቱ ምዕመናኑን በማስተማር የታወቁ በመሆናቸው ከሽማግሌዎች ያዩስ ውንና ቋንጃ ቆርጦ ፡ ነፍስ አጥ ፍቶ በጥል ላይ የነበረውን ባለደም ሁሉ በማስታረቅ መልካም ዝና የነበራቸው አባት ነበሩ ። በዚህም ምክንያት ከሩቅ ቦታ ሁሉ በደም የተለያዩ ወገኖች ሲኖሩ እርሳቸው መክረውና አስተምረው እንዲያስ ታርቁ እየተጠሩ በብዙ ቤተሰብ መካከል የጥል ግድግዳ ሆኖ የኖረ ጸብ በማድረቅ የታወቁ አበ ሰላም ነበሩ ። መልአከ ጽዮን ከተወለዱ በትና ካደጉበት ካስተማሩበት ከደ ብረ ጽዮን ግጃመሬ ማርያም በንብ አዝላ ማርያም ሕዝብ ጥያቄ ሌላው የእናት አባታቸው የትወልድ ቦታ ወደሆነችው ንብ አዝላ ለመኖር በመዛወራቸው የደብረ ጽዮን ሕዝብ ሴት ወንድ ሕፃን ሽማግ ሌው ስዕል መስቀል ይዞ በፍትር አስ ገድዶ ወደነበሩበት ቦታ እን ዲመለሱ አድረጉአቸዋል ።

መልአከ ጽዮን ጥሩነህ በጐ ሰው ከማስተማሩ ሥራቸው ጋር ቁም ጽሕፈት አዋቂ ስለነበሩ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ልዩ ልዩ ታላላቅ መጻሕ ፍትን በመጠነኛ ገንዘብ እየጻፉ ለብዙ አብያተ ክርስቲያናት አገል ግሎት እንዲውሉ አድርገዋል ።

መልአከ ጽዮን ጥሩነህ በጐ ሰው በጋብቻ ዓለም ፶፪ ዓመት የኖሩ "እግዚአብሔር አንድ ያደረ ገውን ሰው አይለይ" የሚለውን አምላካዊ ቃል የፈጸሙ ሲሆኑ በ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ባልና ሚስቱ ባደረ ጉት ስምምነት ሁለቱም በአንድ ነት በአንድ ቀን መንኩሰው እራሳ ቸው የቁምስና ማዕረግ ተቀብለ ዋል መልአከ ጽዮን ጥሩነህ በጐ ሰው የ፰ ልጆች አባት ሲሆኑ ሁሉም በሕይወተ ሥጋ ይገኛሉ ሥጋ ለበሰ ፍጡራን ሁሉ የማይ ቀረው ሞት ለእርሳቸው ስለደረሰ በተወለዱ በ፸፫ ዓመታቸው ምንም ሳይታመሙና ሃዕር ሳይበዛባቸው በመኖሪያ ቤታቸው ጸሎት አድር ገው ጋደም ዕንዳሉ ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፹ ዓ.ም ከቀኑ ሰባት ሰዓት ላይ አርፈው ወዳጅ ዘመድ በተገ ኙበት ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ.ም ተወልደው አድገው ባስተማሩበ ትና በተሾሙበት በደብረ ጽዮን ገጃመሬ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጽሟል ።

ከደቀ መዝሙሮቻቸው አንዱ
መምህር ዮሴፍ ዘለቀ

## ዜና ዮሐ አ ....

(ከገጽ ፲፯ የዞረ)

ለመሆን በቅቷል ከእውቀቱና ከማራኪነቱ የተነሣ በርካታ ሰዎች ከተለያዩ ሩቅ አገር እየ መጡ ከትምህርቱ ይካፈሉ ነበር ። ዮሐንስም በየጊዜው ኢዘውትሮ ያስተምር የነበረው በአንጾኪያ አካባቢ በሚገኙ አብያተ ክርስቲ ያናት እየተዘዋወረ ነበር ።

ዮሐንስ አፈወርቅ በዚህ ዓይ ነት አገልግሎት እየሰጠ ቅስናን ከተቀበለ በአሥራ ሁለት ዓመቱ በአንጾኪያ ሆኖ መጻሕፍተ ብሉያ ትንና ሐዲሳትን በሚገባ አብራ ርቶ ተርጉሟል ። በይበልጥም ስለ ፍቅር ስለ ሕግ ስለ ድሆችና ስለ እውነት ሰፋ ያሉ ጽሑፎችን ያስ ፍር ነበር ። ከዚህም የተነሣ ዮሐ ንስ አፈወርቅ ከሰዎች ዘንድ የድ ሆች ጠበቃ የሚል ስም ተሰጥቶ ታል ።

ዮሐንስ በዚህ አገልግሎቱ እየ ደከመ የሚደርሳቸው ድርሰቶች ለብዙዎች በቂ ዕውቀትንና ምክ

(ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል)



# የቅዱስ ላሊበላ ቅርስ

ህንፃው ፊት ለፊት ገጽታው ወደ ደቡብ ያዞረ ነው ። ከዚህ ህንፃ ውስጥ አንዷት የምታስደ ንቅ እንደ ኮከብ ብልጭ የምትል ነገር ከመንበሩ ኢናት ትገኛለች ። በመሠላል ሄደው ሲጠጓት ትጠፋ ለች ። እንደገና ከታች ሲያዩዋት ትበራለች ።

ቤተ ገብርኤል ፡ ህንፃው ዙሪያ ውን ገደል በመሆኑና ጨለማ የበዛ በት በመሆኑ አያጠራጥርም ምድር ቤቱ ዙሪያውን በውሃ የተ ከበበ በመሆኑ መግቢያው አይታ ይም እስከአሁንም ካህናቱ በም ድር ቤት አይገለገሉበትም ምክን ያቱም ውሃው ቢቀዳ መልሶ ይሞ ላል ከአቅም በላይ በመሆኑ ነው ። ከታሪካዊነቱ አንዱ ባህሩ ነው ። ለዚህም ከተለያየ ክፍላተ ሀገር የሚመጡት ኢትዮጵያውያን ምዕ መናን ፡

ቅዱስ ላሊበላ የላስታው ደብር ውስጡ አረንጓዴ ነው ባሕር

እያሉ የገጠሙለት ይህ ህንፃ ጨለማ የበዛበት በመሆኑ በጣም ያስፈራል ። ከመቅደሱ ውስጥ ግራና ቀኝ ሁለት ክፍሎች ሲኖ ሩት በግራ በኩል በትልቅ መዝ ጊያ ተዘግቶ የሚገኘው የሩፋኤል መንበር የነበረበት ነው ይባላል ። አሁን ቱሪስቶች ይገኙበታል ። በዚያም መውጫ ሲመለከቱ ለሚ ናገሯት ቃላት ያጥርባቸዋል ። ከቤተ ገብርኤል ተያይዞ በግራ በኩል ከፍተኛ አምባ አለ ። ይኸ ውም ምንም አፈርና ድንጋይ ያል ተደባለቀበት ጭንጫው በተራራ መልክ የቆመ ደብረ ታቦር የሚ ባል ከተማዋንና ቤተ ክርስቲያኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው ። በዚህ አምባ ስር ከመጨረሻው ከሸልቆው ከውሃው መውረጃ ብቻዋን ከመሬት ተያይዛ በጎንፃ ወጥ የሆነችው አንዲት መስቀል ቆማ ትታያለች ። ይህች መስቀል ከተራራው ሥር ተያይዛ መጣች እንጅ ለቤተ ጊዮርጊስ በጣም ቅርብ ነች የዚች መስቀል ከዚያ ክርስ ብቻዋን መፈጠር ጥሩ የሆነ ታሪክ አላት።

ቤተ ጊዮርጊስ መቸም አሥ ሩም ህንፃዎች በመልክም ፡ በመ ጠንም ፡ በቅርፅም ፡ በይዘትም አንዱ አንዱን አይመስለውም ። በፍፁም አይገናኙም ። አንደኛ ውን አይተን ወደ ሌላው ስንሄድ እንግዳ ይሆንብናል ። ምን ጊዜም አዲሶች እንሆናለን ታዲያ ይህ ህንፃ የመጨረሻ ሥራ በመሆኑ ከሁሉም ለየት ያለ መልክም ቅር ፅም ። አለው ይኸውም በመስቀል አምሳል ከራሱ ላይ በማህተም የታተመ መስሎ ጠቅላላ ቁመቱና ወርዱ የታችኛው መስኮት ተደ ፍኖ ያ የላይኛው ክፍት ሆኖ በመ ሠረቱ "ሐመረ ኖህ" መርከብ አምሳል እያሉ ይጠሩታል ። ህን ፃው በጣም ጠንካራ ከመሆኑም የተነሳ የጨው ባሩድ ፍጹም አል ቀመሰውም ። ትክክለኛ አቋሙን ይዞ እናገኛዋለን ።

ቤተ ጊዮርጊስ ሶስት በሮች ሰባት ደረጃዎች አሥራ ሁለት መስኮቶች ያሉት ሲሆን እንዲ ሁም ለቱሪዝም የሚጎበኙ ሁለት ያልፈራረሱ የጥንት የሰው አፅ ሞች ይገኛሉ ። እንግዲህ የላሊበላ ህንፃዎች የታቻለኝን ያህል በጽ ሁፍ ልገልጽ ሞከርኩ እንጂ በሙሉ እንኳን በጽሁፍ ይቅርና ሄዶ በዓይን አይቶ በአእምሮ ለመ ቅረጽ በጣም አዳጋች ነው ። ቢሆ ንም ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወገኔ ልጠቁመው የምፈልገው በወሬ ከመስማት ይልቅ ከሥፍ ራው ሄዶ አይቶ ቢመለስ መል ካም ነው ። በእውነቱ ይህ የላሊ በላ ህንፃ ዉት አይተን እንደገና ማታ ስንመለከተው ልዩ ህብር ይዞ እናገኘዋለን ። በዓመት ለሚሄ ዱማ ምን ያህል ይለወጥባቸው? ለዚህም ነው ባለ ቅኔው "ሞት ህንፃ ላሊበላ ኩለሄ እንግዳ" የላሊ በላ ህንፃ ሞት ሁል ጊዜ እንግዳ ነው ! ያለው የላሊበላ ህንፃ በታሪ ክነቱ ልዩ ሊያደርገው የሚችለው ከአንድ ቋጥኝ አሥር ቤተ መቅ ደስ መፈልፈል ብቻ ሳይሆን እንደ ማንኛውም ኃውልት ባዕድ የሆነ ጭቃና አፈር ድንጋይ ያልተቀላቀ ለበት ጣራውም ግድግዳውም አንድ ወጥ በሆነ አለት የታነፀ በመሆኑ ነው አንዳንድ የተሳሳተ አመለካከት ያላቸው ሰዎች የላሊ በላን ህንፃ ያነፁት ግብጻውያን ናቸው ይላሉ ። በመሠረቱ ይህ አባባል ከእውነት የራቀ ነው ። ምክንያቱም ግብጾች እንደነዚህ አይነት ህንፃ መሥራት ከቻሉ በሀገራቸው ለምን እጥፍ ድርብ አድርገው አያንፁም ኖሯል? በእር ግጥ በዓለም የታወቀ አሰደናቂ ሀውልት (ፒራሚድ) አላቸው ። ይህ ፒራሚድ የአሥራሩና አለቱ እንዴት በምን እንደወጣ ባለው በጊዜው ሥልጣኔ ባልነበረበት ጊዜ ይህን ያህል ውጤት መገኘቱ በጣም የሚያስደንቅ ነው ። ቢሆ ንም እንደ ላሊበላ ህንፃ ከአንድ



www.ethiopianorthodox.org

ድንጋይ ወጥ ሆኖ አልተሠራም ። ከተለያየ ቁሳቁስ መሆኑ ለማንኛውም ግልጽ ነው ። ታዲያ የላሊበላ ህንፃ ጣራውም ግድግዳውም መስኮቶችም ቅርጹም ደረጃውም በአንድ ደንጊያ የተጠቃለሉ ናቸው ። እንዲሁም የህንፃዎቹ ታሪክ ከሃይማኖት ጋር ተያይዞ የተሠራ እንደመሆኑ ሄዶ በዓይን በብረቱ ያየ ሁሉ ፍርዱን እንደሚሠጥ አልጠራጠርም ።

በነገራችን ላይ የላሊበላን ከተማና ህንፃዎች ትውስታ ያዞረኝ ያህል በመጠኑ አስተዋውቄዋለሁ ። እስቲ ደግሞ አሁን የባህሉን ማለትም የካህናቱንና የአካባቢውን ህብረተሰብ የዓመት በዓል ወገና ሥርዓት ላውጋችሁ ። የላሊበላ ካህናት ቁጥራቸው በግምት ወደ ፲፻ እንደሚደርስ ያታወቃል ። ሆኖም በአንድ አስተዳዳሪ በአንድ መሪ ጌታና ሊቀ ካህናት መሪነት የሚተዳደሩ ናቸው ። ካህናቱ አብዛኛውን ኑሩዋቸው በግብርና የተመሠረተ ነው ። ከነኝህም መካከል ብዙዎቹ የፀዋትወ ዜማና የቅኔ የአቋቋም የድጓ የብሉይና የሐዲስ መጻህፍት መምህራን ሊቃውንት ይገኙበታል ። ካህናቱ በክብረ በዓል ጊዜ የተለመደ ዩኒፎርማቸውን ለብሰው በሚያሸበሽቡበት ጊዜ ህንፃውንና እነሱን የተመለከተ በልዩ የተመሰጦ ባሕር ይዋኛል ። በተለይ ታህሣሥ ፳፱ ቀን የክርስቶስ ልደት እንደመሆኑ መጠን አጼ ላሊበላ በዚሁ ዕለት የተወለደ ስለሆነ እነኚህ ካህናት ጥንግ ድርብ ፡ ሸማ ጃኖ ፡ ካባ ፡ የለበሱ በመከታተል "ከማሜ" ጋራው ላይ ይወጣሉ። ጠቅላላ ህዝቡ እታች የጠጠር ማረፊያ እስከሚጠፋ ተጨናንቆ ይቀመጣል ። እላይ ሆነው "ቢዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ" እያሉ በአማረ ድምጽ በተዋበ መሀረም መቋሚያቸውን ይዘው ሲያዜሙ ከታች ካሉት ጋር እየተቀባበሉ የላይኞቹ በሚሰግዱበት ጊዜ ልክ ከሰማይ ርግፍ የሚሉ ይመስላሉ ። ሰው መሆናቸው ያጠራጥራል ። በዚህ ጊዜ ነው ቤተ ማርያም በልልታና በጭብጨባ የምታስተጋባው ። ቦታውን አጨናንቆ የያዘው ምዕመናን በዚህ ጊዜ ነበር "ዓይኔ ዓለም አየ እግሬ ደርሶ የድንጋይ ወጋግራ የድንጋይ ምሰሶ" እያሉ የሚዘፍኑት ይህ ማህሌት በሚቀጥልበት ጊዜ ለበዓሉ ከፍተኛ ድምቀት ይሰጠዋል። በዚህ ሰዓት ቱሪስቶች ፎቶግራፍ ለማንሣት ግራ ይገባቸዋል። ካህናቱ ሊደነቁ የሚገባቸው በዚህ የማይደርሳ ትወስታዎች ነው። የዜማውን አጣጣልና የአሸባሸቡን ይዘት በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ ከአቅም በላይ ነው ። ቢሆንም ከቦታው ባህል ጋር አብሮ የሚሄደውን የዜማ አጣጣል ከካህናቱ አንድ የድምጽ ተውህቦ ያላቸው ርዕሰ ደብር ገብረ መስቀል አማኙ የተባሉት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ ሐዋርያዊ ድርጅት መምሪያ ያስቀረጹትን መዝሙሩ ማዳመጥ ይቻላል ። ቱሪስቶች በጉብኝት ከሚቀስሙአቸው የካህናቱ ያሬዳዊ ሽብሸባና ማህሌት ነው ።

ዲያቆን በየነ ድንቁ

## ዜና ዮሐ አ ....

(ከገጽ ፰ የዞረ)

ርን የሚሰጡ ሲሆኑ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎትም ድርሰቶቹ በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም እንዲሰጡ አድርጓል ።

በዮሐንስ ድርሰቶች ላይ በቁዕውቀት ያዘሉ ጽሑፎች ብቻ ሳይሆኑ ስለ እኩልነትና ስለ አንድነት አጥብቀው የሚገልጹ ናቸው ።

እንግዲህ ከእንደዚህ ዓይነቱ ታላቅ አባት የምንማረው ራስን በእውቀት ማሳደግ እንዲሁም ስለ እኩልነትና ስለ ፍቅር አጥብቀን ልናውቅና እውነትን ልንመሰክር እንደሚገባ በአገልግሎታችንም መትጋት እንደሚገባን ያሳስበናል።

ይህ ታላቅ አባት ዮሐንስ አፈወርቅ በዚህ መልካም ምግባሩ ቢመሰገንም በአንዳንዶች ሰዎች ደግሞ በደረሰበት ተቃውሞ በስደት ላይ ሳለ መስከረም አሥራ አራት ቀን ፬፻፯ ዓ ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል ።

ቅንነትንና እውነትን የዘወትር ዓላማቸው አድርገው የሚኖሩ ሰዎች በሥጋ ቢሞቱም በመልካም ስራቸው ዘወትር ሲታወሱ ይኖራሉ ። የዚህንን ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አባት ፈለግ በመከተል ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን የሚገኙ ሊቃውንት አባቶቿ በመጻሕፍቱና በድርሰቱ በመገልገል ስለ ሰላምና እኩልነት ያላቸውን አቋም እያንጸባረቁ ነው ።

ስለዚህ ዮሐንስ አፈወርቅ የነበረውን እውነተኛ አቋም ሁላችንም ተከትለን እርሱ የድሆች ጠበቃ ፡ እንደተባለ እኛም ለሌሎች ባለን መልካም ምሳሌና አር

(ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል)



# ትንሣኤና ሕይወት

የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በትንቢት የተነገረ በሐዲስ ኪዳን የተሰበከ ከዚያም በምሳሌ የተገለፀ ነው ፈጣሪ ዓለማት ጌታ ወደዚህ ዓለም ከመምጣቱና ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ ነቢዩ ዳዊት "እግዚአብሔር ይነሳል ጠላቶቹም ይበተናሉ እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሳ ጠላቶቹንም በኋላው መታ" በማለት ሙስና መቃብርን አጥፍቶ እንደሚነሳና ጠላቶቹ አይሁድም በትንሣኤው እንደሚያፍሩ በትንቢቱ ተናግሮ ነበር ።

ወንጌላዊ ማርቆስም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቃል ሲገልጽ የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል ከሽማግሎችም ፡ ከካህናት አለቆችም ፡ ከጸፎችም ሊጠላ ሊገደልም ከሶስት ቀን በኋላ ሊነሳ እንዲገባው ያስተምራቸው ጀመር ቃሉንም ገልጦ ይናገር ነበር ማር ፰፡፴፩—፴፪ ፤

ይሁን እንጂ የክርስቶስ ሞት ለዓለም ሕይወት እንደሆነና የተቀበለው ጸዋትወ መከራም የድኅነት መገኛ ፡ ለሰው ልጆች ሰላም መሆኑ የተረጋገጠው ሶስት መዓልት ሶስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ በተነሣው ትንሣኤ ነው።

ይህንን የክርስቶስ ትንሣኤ አብነት በማድረግና በእርሱ በራሱ ቸርነት የሰው ልጅ በዚህ ውጣ ውረድ በበዛበት ዓለም ሲኖር ዕለተ ሞቱ ደርሶም ይሁን ሳይደርስ ወደደም ጠላም በሞት ከዚህ ዓለም ይለያል ኋላ ግን ሕይወት ያለው ዘለዓለማዊና ህያው ሆኖ እንደሚኖር ፡ በትንሣኤ ሙታንም በሐዲስ ትንሣኤ እንደሚነሣ የተረጋገጠው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው ። ማንም ሳያስገድደው የአዳም ልጆችን ለማዳን ሰው ሆኖ በፈቃዱ እንደሞተ በፈቃዱም እንደተነሣ ቀደም ብሎ ለደቀመዛሙርቱ "ነፍሴን እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ማንም ከእኔ አይወስዳትም ላኖራትም ላነሳትም ስልጣን ያለኝ እኔ ነኝ ሲል በፈቃዱ ሞቶ በስልጣኑ እንደሚነሳ ነግሮአቸዋል ።

ስለዚህም እነርሱ አይተውት ትንሣኤውን አመኑ ፡ ጥርጥርና ፍርሃትም ጠፋላቸው እነርሱም የሰሙትንና የአዩትን ለሌሎች በመናገር ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ እንደተነሳ ሁሉ ሰዎችም እንዲሁ እንደሚነሱ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በአስተላለፈው መልእክቱ አስገንዝቦናል ፡ "ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ ፡ ተቀበረ በሶስተኛውም ቀን ተነሳ ለኬፋም ታዩ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ ከዚያም ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታዩ ስለዚህ ክርስቶስ ለአንቀላፉት ሁሉ በኩር ሆኖ ከሙታን ተነስቷል ፡ ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታንም እንዲሁ በሰው በኩል ሆኖአልና ሁሉ በአዳም እንደሞቱ ደግሞ በክርስቶስ ሕያዋን ይሆናሉ ፩ ቆሮ ፲፭፡፫

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መቀበሉ ፡ መሞቱ መነሳቱ እኛ በደለኞች የሆነውን ሁሉ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ለመመለስ ነው ። በተጨማሪም ሞትን ድል አድርጐ መነሳቱ ለሰው ልጆች ድህንነትን ለማጐናጸፍና አምላካዊ ፍቅሩን ለእኛ ለመግለጽ እንዲሁም ደግሞ በደላችንን ያስወግድልን ዘንድ መሆኑ መታወቅ አለበት ።

በመሆኑም ሕይወታቸውን ሁሉ ለእርሱ የሰጡ በምግባር በሃይማኖት የጸኑ ወዳጆቹ ጻድቃንን ትንሣኤ ዘለክብር ያስነሳቸውና ያጸድቃቸው ዘንድ ሞትን ድል አድርጐ የተነሳበት ዋናው ምክንያት ይህ ነው ።

ስለዚህም ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝም ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ። ህያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘለዓለም አይሞትም በማለት ዮሐንስ በወንጌሉ ፲፩፡፳፭ ላይ ክርስቶስ ትንሣኤና ሕይወት መሆኑን አንድ በአንድ ያስረዳን ፡ በእርግጥም ለሚያምንበት ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤና ሕይወት ነው ።

እንግዲህ ከዚህ ላይ የምናስተውለውና የምናጤነው ነገር ቢኖር ክርስቶስ ሞቶ ከሙታንም ተለይቶ በመነሳት ለሚሞተው ሰውነታችን የዘለዓለም ሕይወት እንድናገኝ አድርጐናል ትንሣኤን የምናከብረውና የምንመለከተው በምን መልክ ነው ? በመብል ፡ በመጠጥ ፡ አዳዲስ ልብስ በመልበስ ፡ በጠቅላላው ሥጋዊ ነገሮችን ብቻ በመፈጸም ከሆነ እኔ ትንሣኤም ሕይወትም ነኝ ያለውን ቃል



www.ethiopianorthodox.org

በተግባር አልተረጎምነውም ማለት ነው ይህንንም ስንል መብላት ፡ መጠጣት ፡ መልበስ ኃጢአትና በደል ያመጣል ማለታችን አይደለም ። በመጠን መኖር ሲገባን በትንሣኤ በዓል ምክንያት ከማን አንሼ በማለት ከአቅማችን በላይ ድግስ በመደገስ ከፍተኛ ገንዘብ በማውጣት ፡ ከአጣንም በመበደር ለአንድ ቀን ደስታ ስንል የብዙ ቀን መቆያችንን ወይም ጥሪታችንን አባክነን ራሳችንንም ሆነ ቤተሰቦቻችንን ከችግር ላይ መጣላችን ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ሲጽፍ "ወንድሞች ሆይ የጨለማ ልጆች አይደላችሁም የብርሃን ልጆች የቀንም ልጆች ናችሁና እኛ ከሌሊት ወይም ከጨለማ አይደለንም ፡ እንግዲያስ እንንቃ በመጠንም እንኑር" ተሰሎ ፩·ም·፭·፭ ብሏል ።

ትንሣኤም ስንል የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ የምናስብበት ፡ ስለኛ ብሎ የተቀበለውን መከራ መስቀሉን ዘወር ብለን የምናስታውስበት ፡ ሰላምና ሞገስ ያገኘን በት ዕለት መሆኑን የምንሰብክበት ቀን እንጂ አብዝቶ በመብላትና በመጠጣት የምንውልበት አለመሆኑን ልናውቅ ይገባል ይልቁንም ሲጾሙና ሲጸልዩ ለቆዩት ድሆች ያለንን የምናካፍልበት ፡ እንደኛው ጾም እንዲፈቱ የምናደርግበት ትንሣኤያችን ነው የሞት መውጊያ ኃጢአትም ኃይል ህግ ቢሆንም ክርስቶስ በትንሣኤው ድል ስለአሸነፈልን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሳትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ።

እንዳወቀ ቢተው

# ደብዳቤዎች

( ከገጽ ፩ የዞረ)

ንም ወደፊትም ሰበካ ማለት አጥቢያ ጉባኤ ማለት አንድነት ሲሆን በጥቅል ሲፈታ የአጥቢያው ወይም የሰበካው ምእመናንና ምእመናት አንድነት ማለት ነውና ላላወቁት ማሳወቅ ላልተረዱት ማስረዳት ይገባናል ።

፬ኛው ጥያቄህ ቄሱ ጥፋተኛውን ምእመን ከስሕተቱ እንዲታረም ቢያወግዘው መልሶ ማውገዝ ይገባዋልን የሚል ነው ። ቄስ ሥልጣነ ክህነት ያለው በመሆኑ ለማሠርና ለመፍታት ሥልጣን ከክርስቶስ ተሰጥቶታል ። የማሠርና የመፍታት ሥልጣን አለው ስለዚህ ቄሱ ከክርስቶስ በተሰጠው ሥልጣን ሲያወግዝ ምእመኑ በማሃይምን ቃሉ ቢያወግዘው በፍጹም ሊያሥር አይችልም። ምንም ሥልጣን የለውምና። እንዲያውም ሥልጣን ሳይኖረው ካወገዘ ኃጢአት ነውና ንስሐ መግባት አለበት ።

በ፭ኛው ጥያቄህ ላይ ደግሞ ክርስቶስ በአይሁድ እጅ ተይዞ ሊሰቀል ወደ ቀራንዮ አደባባይ ሲወሰድ ቅዱሳት ሴቶች ደረታቸውን እንደደቁ ጠቅሰህ ይህን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ትቀበለዋለች ወይ? ብለህ ጠይቀሃል ፡

በወንጌል ተጽፎ እንደምናገኘው ቅዱሳት አንስት ደረታቸውን እየደቁ ኢያለቀሱ ክርስቶስን ተከትለውታል ። ግን የእነርሱ ደረት አደቃቅና የእኛ የተለያየ መልክ አለው ። መጽሐፉ ደረታቸውን ደቁ ማለቱ እንደ እኛ እናቶችና እህቶች ወደላይ እየዘለሉ ደረትን እንደከቦሮ መደብደብ ሳይሆን ከልብ እያዘኑ እንባቸውን በደረታቸው ላይ እያፈሰሱ ተከተሉት ማለት ነው ። አሁንም ቤተ ክርስቲያናችን ደረት መድቃትን ፊት መንጨትን በጥብቅ ትቃወማለች እንጂ አትቀበለውም ፡

በመጨረሻም ጥያቄህ ለሰንበት ት/ቤት ተማሮች በሌሎች አህጉረ ስብከት ሴሚናር ሲደረግ በጋሞ ጎፋ ሀ ስብከት ለምን አልተደረገም የሚል ነው ። በእርግጥ በመላው ሳይሆን በአንዳንድ አህጉረ ስብከት ለሰንበት ተማሪዎች ሴሚናር መደረጉ የታወቀ ነው ። በተራ ስለሆነ ለሁሉም ይደርሰዋል ፡ ሴሚናር ካልተደረገላቸው አህጉረ ስብከት አንዱ ጋሞ ጎፋ ነው ። ይኸውም ሀገረ ስብከቱን በመዘንጋት ሳይሆን ተራው ስላልደረሰው ነው ። ተራ በደረሰው ጊዜ ሴሚናሩ በእናንተም ሀገረ ስበከት ስለሚደረግ እስከዚያው ጠያቂውዲያቆን ገዛኸኝ ደረስ በትዕግሥት እንድትጠባበቅ እናሳስባለን ።

## ዜና ዮሐ አ ....

(ከገጽ ፳፪ የዞረ)

አያኑት በአገልግሎታችን የምን መሰገን ሆነን እንድንገኝ የዚህን ታላቅ አባት አርአያነት መከተል አለብን ።

በመልካም ሥራችን የቤተ ክርስቲያን ልጆች ለመባል እንበቃለን በዚህ በተጠራንበት ዓላማ ጸንተን መቆም ይገባናል ።

መምህር ተወልደ መድኅን

ገ ሥላሴ





# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።
ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቁ.
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org